ልዩ ዕትም

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3590 | አርብ መስከረም 1 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር

# አዲሱ ዓመት

## "የጉባ ብሥራቶችን የበለጠ ተግባራዊ የምናደርግበት ዘመን ይሆናል"

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በጋዜጣዋ አዘጋጆች**

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ቀጣዩ ዓመት የጉባ ብሥራቶችን የበለጠ ተግባራዊ የምናደርግበት ዘመን ይሆናል ሲሉ ተናገሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የ2019 ዓ.ም ዘመን መለወጫን አስመልክቶ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ቀጣዩ ዓመት የፖለቲካ ምኅዳሩ ሰፍቶ የተለያዩ ዕሳቤዎችንና አካሄዶችን በብሔራዊ ጥቅም አስተሣሥረን የምንጓዝበት ዓመት ይሆናል ብለው፣ ዓመቱ የጉባ ብሥራቶች የበለጠ ተግባራዊ የሚደረጉበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሙሉ መልዕክት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ዘመን ከፈጣሪ ለሰው የተሰጠ የመሥሪያ መጽሐፍ ነው። ይህ የመሥሪያ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጡ የተወሰኑ ገጾች አሉት። የመጨረሻው ገጽ ተጠናቅቆ የማጠቃለያው ሽፋን እስኪከደን ድረስ የፈለግነውን የመጻፍ መብት በእጃችን ነው። አንዳንዶች ዓለምን የቀየሩ ሐሳቦችንና ሥራዎችን፤ ሌሎች ታሪክን የቀየሩ ዕሳቤዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ጽፈውበታል። በተቃራኒው ዓለምን ያወደሙ፤ ሕዝብ የከፋፈሉና የጨረሱ፤ ተፈጥሮን ያዛቡ፤ ክፋትንና ጭካኔን ያስተማሩ ሐሳቦችንና ተግባራትን የጻፉበትም ጥቂት አይደሉም።

ኢትዮጵያውያን በዚህ የዘመን መጽሐፍ ውስጥ ምን እየጻፍን ነበር? አሁንስ ምን እየጻፍን ነው? ወደፊትስ ምን ለመጻፍ እናስባለን? ከኋላችን ያሰናበትነው አሮጌ ዓመት እና ከፊታችን የምንቀበለው አዲስ ዓመት እነዚህን ጥያቄዎች እንድንመልስ ያስገድዱናል። ዓለምን ያስደነቁ የንግድ፣ የግብርና፣ የሥነ ሕንጻ፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የሥነ ከዋክብት፣ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር፣ ሥነ ሥዕልና ሥነ ዜማ፣ ኃይማኖትና ፍልስፍና - በዘመን

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

# "አዲስ አበባ ጊዜዋን አላባከነችም"

**የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በጋዜጣዋ አዘጋጆች**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2019 አዲስ ዘመን መለወጫ በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፣ ከተማዋ አዲስ ዘመን በተቀበለች ቁጥር ጊዜዋን ሳታባክን እንደ አደይ አበባ እየፈካችና አዲስ ገጽታን እየተላበሰች መምጣቷን ገልጸዋል።

አዲስ አበባ አሮጌና የተጎሳቆሉ ገጽታዎቿን ከአሮጌው ዘመን ጋር በመሸኘት፣ የ365 ቀናት፣ የ24 ሰዓታት እና የሳምንቱን ሰባቱን ቀናት ሙሉ ጥረት በመጠቀም የሥራ ባህል መገንባቷን አብራርተዋል። ይህ ጥረትም ከተማዋን የትጉሃን መዳረሻ፣ የዓለም አቀፍ መስህብና የዜና ምንጭ ወደ መሆን አሸጋግሯታል።

አሁን ላይ ስለ አዲስ አበባ አዳዲስና አዎንታዊ ዜናዎችን መስማት የተለመደ መሆኑን ያነሱት ከንቲባዋ፣ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ቅድሚያ የምትሰጥ መሆኗን ገልጸዋል። በተለይም በሰው ተኮር ሥራዎቿ ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ጉድለት በመሸፈን፣ የተረሱትን በማስታወስና ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ላይ አተኩራለች። በተጨማሪም አዲስ አበባ የኢትዮጵያውያን መኖሪያ ብቻ ሳትሆን የብዙ ዲፕሎማቶችና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ፣ ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ወደፊት እየተጋች ትገኛለች።

በማጠናቀቂያው ዘመን የተከናወኑ ተግባራት ለቀጣዩ ዘመን ጠንካራ መሰረት መጣላቸውን ያመለከቱት ከንቲባ አዳነች፣ ሀገሪቱ 7ኛውን ሀገራዊ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# በዓሉን ስናከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ ሊሆን ይገባል ተባለ

**በጋዜጣዋ አዘጋጆች**

የአዲስ ዓመት በዓልን ስናከብር በመተጋገዝ እና የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ ሊሆን ይገባል ሲሉ የኃይማኖት አባቶች ተናገሩ፡፡

የ2019 ዓ.ም የአዲስ ዓመት በዓልን አስመልክቶ የኃይማኖት አባቶቹ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፣ በዓሉን በአንድነት በመቆም ለተራቡት፣ ለተጠሙት፣ ለታረዙትና ለታመሙትም ሁሉ ካለን ከፍለን በመስጠት ከእኛ ጋር በመንፈስና በሞራል እንዲያሳልፉ እናድርግ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለኃይማኖት፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳትና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊ ጳጳሳት ጉባዔ ፕሬዝዳንት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል እና የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ዋና ጸሐፊ ቄስ ደረጀ ጀንበሩ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

መልካም አዲስ ዓመት!!

# ርዕሰ አንቀፅ



## አዲሱ ዓመት፤ አዲስ አበባ በስኬትና በብሩህ ተስፋ የምትቀበለው ነው!

አዲስ ዓመት ለኢትዮጵያውያን የአዲስ ተስፋ፣ የአዲስ ጅማሬና የአዲስ ትጋት ምልክት ነው። አዲስ ዓመትን ስንቀበልም ያለፈውን ዓመት በማስታወስ የተገኙ ውጤቶችን ማየትና ቀጣዩን ዓመት በብሩህ ተስፋ መጀመር ይገባናል። በተለይ አዲስ አበባ የምትቀበለው አዲሱ ዓመት በከተማዋ ገጽታ፣ በነዋሪዎቿ ኑሮና በአገልግሎት አሰጣጧ ላይ እየታዩ ካሉ ለውጦች የተነሳ ልዩ ተስፋን የሚያጭር ነው። ያለፈው ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ ሰፊ ስራዎች የተከናወኑበት ነው። የኮሪደር ልማት ስራዎች ከተሽከርካሪ መንገድ ግንባታ ባሻገር የእግረኛ መንገድ፣ የብስክሌት መስመር፣ የሕፃናት መጫወቻ፣ የመዝናኛ ቦታና የመኪና ማቆሚያን በአንድ የከተማ እቅድ ውስጥ አጣምረዋል።

የወንዝ ዳርቻ ልማትም ከተማዋን ለነዋሪዎቿ የተሻለች ለማድረግ የተያዘውን ርዕይ ያጠናክራል። እድገቱም በዓለም ከተሞች የሚታየውን አዲስ አቅጣጫ የተከተለ ነው፤ ከተሞች የወንዞቻቸውን ዳርቻ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ ለመዝናኛ፣ ለጤናና ለቱሪዝም ሀብት እያዋሉት ነው። ስለዚህ የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት የዛሬን ብቻ ሳይሆን የነገን ከተማ ለመገንባት የሚያስችል ዕድል ነው። በነዋሪዎች የኑሮ ጫና ውስጥ ከባዱ ጉዳይ ከሆነው መኖሪያ ቤት አንፃርም የተጀመሩ ሥራዎች ተስፋ የሚሰጡ ናቸው። ዓለም አቀፍ የመኖሪያ ቤት ቀውስ በእጅጉ እየጠነከረ ሲሆን፣ በ2023 እስከ 3 ነጥብ 4 ቢሊዮን ሰዎች አስተማማኝና በቂ መኖሪያ እንደሌላቸው ተመድ መኖሪያ ቤትን በተመለከተ ያወጣው ሪፖርት ያሳያል። በዚህ ዓለም አቀፍ ፈተና መካከል አዲስ አበባ በተለያዩ የከተማዋ ክፍሎች ቴክኖሎጂን በመጠቀምና የ24/7 (ሳምንቱን በሙሉ ሃያ አራት ሰዓት) የስራ ባህልን በመተግበር በርካታ ቤቶችን በመገንባት ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ደግሞ የበርካቶችን የቤት ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡

አገልግሎትን ለነዋሪው ፈጣንና ተደራሽ ማድረግ የከተማዋ የለውጥ አንዱ ጠንካራ ጎን እየሆነ ነው። “አዲስ መሶብ” አንድ የከተማዋ ነዋሪ በተለያዩ ቢሮዎች በመመላለስ ጊዜና ገንዘብ ከሚያጠፋበት አሠራር ወደ ተቀናጀ፣ ዲጂታልና ተገልጋይን መሠረት ያደረገ አገልግሎት ወደ መስጠት ለመሸጋገር የተወሰደ እርምጃ ነው። እስከ ሰኔ 2018 ዓ.ም ድረስም አገልግሎቱ ወደ ሁሉም ክፍለ ከተሞች ተዳርሷል፡፡ አዲሱ ዓመትም ይህ ስኬት ይበልጥ የሚያድግበትና በብሩህ ተስፋ እንድንቀበለው የሚያደርግ ሌላኛው ስኬት ነው፡፡ የከተማ እድገት አንዱ የሚለካበት በሚፈጠረው የሥራ ዕድልና በሚንቀሳቀሰው ኢኮኖሚም ጭምር ነው። አዲስ አበባ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር በላይ ካፒታል ኢንቨስትመንት መሳብ መቻሏ፣ 22 ሺህ 190 አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችንና 1 ሺህ 632 የማስፋፊያ ፈቃዶችን መስጠቷ የከተማዋን የኢኮኖሚ አቅም ያሳያል። ከአዳዲሶቹ ፈቃዶች ከ54 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ የሆነና ለበርካቶችም የስራ እድል የፈጠሩ ሆነዋል፡፡

ስለዚህ አዲሱን ዓመት ስንቀበል የተሠሩትን ሥራዎች በማድነቅ ብቻ ሳንቆም፣ የተጀመሩት ሥራዎች በተሟላ ጥራትና ፍጥነት እንዲጠናቀቁ፣ ጥቅማቸውም ለሁሉም ነዋሪ እንዲደርስ በጋራ ልንሠራ ይገባል። አዲስ አበባ በአፍሪካ የተሻለ የኑሮ፣ የሥራ፣ የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም መዳረሻ የመሆን አቅሟ ከፍተኛ ነው። የከተማዋ ለውጥ ግንባታውን በሚያካሂዱ አካላት ብቻ የሚጠናቀቅ አይደለም፤ በነዋሪዎቿ ተሳትፎና በከተማዋ ላይ ባለን የጋራ ኃላፊነት መደገፍ አለበት። እናም አዲሱ ዓመት ለአዲስ አበባ የተሻለ ከተማን ለመገንባት የተሰጠን አዲስ ዕድል ነው፤ ባለፈው ዓመት በተገኙ ስኬቶች ተነሳስተን፣ በቀጣዩ ዓመት በበለጠ ትጋት ከሠራን የምንመኛትን የተሻለች፣ ውብ፣ አረንጓዴና ለሁሉም የምትመች አዲስ አበባን መገንባት እንችላለን። መልካም አዲስ ዓመት!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ትኩረት የሚሻው የበዓል ማግስት የስራ ቀናት ውሎ

**በሰናይ ምግባሩ**

በቅድሚያ እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም፣ በፍቅርና በጤና አደረሰን። በኢትዮጵያውያን ዘንድ በዓላት የመሰባሰቢያ፣ የመጠያየቂያ፣ የፌሽታ ሆነው የሚከበሩ እና ልዩ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህን መልካም እሴት የበለጠ እያጎለበቱ መሄድ ይገባል የሚለውን አስተያየቴን በእግር መንገድ ጠቀስ አድርጌ ወደ ዋናው እይታዬ ልግባ፡፡ ሀሳቤን ማጋራት የፈለግኩት የዛሬው ጉዳይ በበዓላት ማግስት የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውሏችን ምን ይመስላል? የሚለው ነው፡፡

እኔ በትዝብቴ እንዳየሁት፣ ሚዲያዎች በዘገባቸው እንዳመላከቱት፣ ከበዓል በኋላ ባሉት የስራ ቀናት ባለሙያው ሰዓቱን ጠብቆ በመግባት በአግባቡ ማገልገል ላይ ቀላል የማይባል ውስንነት አለ፡፡ ሰዓት ሸርፎ መምጣት፣ አስቀድሞ መውጣት አለፍ ሲልም ከነአካቴው መቅረት ይስተዋላል፡፡ ይህ ተገልጋዮችን ላልተገባ መንገላታት፣ የጊዜ ብክነትና የትራንስፖርት ወጪ ይዳርጋል፡፡ አሁን ከተማችን እየተከተለችው ካለው የስራ እሳቤ ውጭም ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማችን ሳምንቱን በሙሉ ሃያ አራት ሰዓት እየተሰራ ዓለም የመሰከረለት ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡ የንግድ፣ የትራንስፖርት እና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በምሽትም ጭምር አገልግሎት መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ጭምር ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ሰበብ እየፈለጉ መስራት ከሚገባው ስምንት ሰዓት መሸራረፍ ተገቢነት ስለሌለው የመንግስት ሰራተኞች እንደ አንድ የ2019 ዕቅድ ይዘውት ከዚህ አይነቱ አዙሪት ውስጥ መውጣት አለባቸው ብዬ አስባለሁ። ይህን ስል ግን በአርዓያነት ሊጠቀስ የሚችል የሰዓት አጠቃቀም ያላቸው፣ አይደለም ስምንት ሰዓት ከዚያ ዘለግ ያለ ጊዜ አምሽተውና አድረው ጭምር የሚሰሩ ሰራተኞች እንዳሉ ግን ልብ ይሏል፡፡ በተጨማሪም በዓመት እረፍት ምክንያት ሊቀሩ የሚችሉት ይህ አስተያየቴ የማይመለከታቸው መሆኑን መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

በሌላ በኩል የክፍሉ ኃላፊዎች ራሳቸው አርዓያ ሆነው በሰዓት መገኘት፣ ሰራተኞቻቸው እንዲገኙ ማድረግ፣ በተለያየ ምክንያት ባልተገኙት ላይ አስተማሪ እርምጃ መውሰድ እና ባለመኖራቸው ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ክፍተት መሙላት ይጠበቅባቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

በአጠቃላይ “ደንበኛ ንጉስ ነው” ካልን፣ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን መድፈን ካስፈለገ በአገልጋዩ ሰራተኛ ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ የሚያመጣ ግንዛቤ መፍጠር ይገባል፡፡

ይህ ሲሆን አገልግሎቱን ከቴክኖሎጂ ጋር የማስተሳሰሩ ነገር የበለጠ ፍሬ እያፈራ ይመጣል፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እና ሦስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መቀመጫ መሆኗ ተከትሎ ያለውን የተለያየ የማህበረሰብ ክፍል የሚመጥን ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ? ሀሳባችሁን ተለዋወጡ እያልኩ በድጋሜ መልካም በዓል ተመኘሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

# አዲሱ... ከገጽ 1 የዞረ

መጽሐፋችን ውስጥ የጻፍንባቸው የዘመን ገጾች አሉን። በተቃራኒው ረሃብና ቸነፈር፣ ጦርነትና እልቂት፣ መከፋፈልና መለያየት፣ ማነስና መድከም፣ የጻፍንባቸው የዘመን ገጾችም አሉን።

የትናንቱ ዘመን ጠባሳውንም ዐሻራውንም፣ ዕዳውን ምንዳውንም ሰጥቶን አልፏል። አሁን ወሳኙ ነገር በቀሩን ዘመናት ምን ቁም ነገር እንሰራለን? የሚለው ነው።

ኢትዮጵያውያን ዛሬ ለትውልድ የሚተርፍ አስደናቂ ታሪኮችን እየሰራን ነው። አረንጓዴ ኢኮኖሚን በአረንጓዴ ዐሻራ፤ ቱሪዝምን በገበታ ፕሮጀክቶች፤ የምግብ ሉዓላዊነትን በበጋ ስንዴና በሌማት ትሩፋት፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን በኢትዮጵያ ታምርት እየገነባንና እያጸናን ነው። የኢነርጂ ዐቅማችንን በተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክትና ኑክሌር ቴክኖሎጂ ለማሳደግ፤ የአፈር ማዳበሪያ ግብአቶችን በሀገር ውስጥ ለመሸፈን፤ የአየር መንገድ አድማሳችንን በግዙፉ የቢሾፍቱ አየር ማረፊያ ፕሮጀክት ለማስፋት፣ ነገን አስበን ዛሬ እየተጋን ነው።

የሕዳሴ ግድብን ፍጻሜ፤ የመስኖ ግድቦችን ፍሬ፤ የሩዝ ምርትን ከፍታ፤ የፍራፍሬ ምርትን ተአምር፤ የወጪ ንግድን ጭማሬ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያችንን ውጤት፤ በአፍሪካ የፈጠርነውን የኢነርጂ ትሥሥር፤ ዲጂታል 2030ን ስኬት፤ የኮሪደር ልማታችን የኢትዮጵያን ሀብትና ውበት መግለጥ፤ የዘመን መጽሐፋችን እየመዘገበ ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማታችን አፈራችንንም፣ ከተማችንንም፣ ጤናችንንም፣ ውኃችንንም እየጠበቀ መሆኑን፤ መድኃኒት የማምረት ደረጃና ዐቅማችንም እያደገ መሄዱን፤ የማዕድን ፍሊጋችን፣ ምርታችንና ሽያጫችን የዘመናት ስብራትን እየጠገነ መምጣቱን፤ የባሕር በር አጀንዳችን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ማግኘቱን፤ የኢትዮጵያ የተጽዕኖ አድማስ መስፋቱን - የዚህ ዘመን የመጽሐፉ ገጾች እያሠፈሩ ናቸው።

እነሆ የዘመን መጽሐፋችንን የ2019 አዲስ ምዕራፍ የምንጀምረው ሀገራዊ ምክክራችንን በስኬት አጠናቅቀን ነው። ይሄንን ምክክር ለዘመናት ኢትዮጵያውያን ይጠይቁት ነበር። ችግራችንን በጦርነት ከመፍታት ይልቅ ለምን አንመካከርም ይሉ ነበር። በየብሔረሰቡ ያለውን የመነጋገርና የመመካከር ባህል ለምን ወደ ፖለቲካው አናመጣውም ይሉ ነበር።

የዘመን መጽሐፍ ገጾችን ስናነባቸው ይሄን ጥያቄ ያቀረቡ ወገኖች ብዙ ዋጋ መክፈላቸውን ያስነብቡናል። እኛ ግን ሐሳቡን አመንበት፤ አምነንም ተቀበልነው፤ ተቀብለንም ተገበር ነው። ማመናችንና መተግበራችን ትክክል እንደሆነ የሚያሳዩ ውጤቶችንም ምክክሩ አስገኘልን።

የመጀመሪያው ውጤት "የጠላት ሟርት መክሸፉ" ነው። ኢትዮጵያውያን ሊመካከሩ አይችሉም፤ ቢመካከሩ ወደ ተቀራራቢ ሐሳብ አይደርሱም የሚለውን ሟርት አክሽፈነዋል። ለመመካከር እንደምናቅድ፤ አቅደን እንደምንጀምር፤ ጀምረን እንደምንጨርስ በሀገራዊ ምክክር አስመስክረናል። ብዝሃ ሐሳቦቻችን በሀገር ጉዳይ የጋራ አቋም ከመያዝ እንደማያግዱን በተግባር አይተናል።

ሁለተኛው "ባህሉ" ነው። ከፀሐይ በታች ባሉ ጉዳዮች የመወያየት፣ የመነጋገርና የመግባባት ፖለቲካዊ ባህልን ማዳበራችን ታላቅ ስኬት ነው። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የልሂቃን ጉባኤ አድርጋ ይሆናል። ለሕዝቡ "እኛ እናውቅልሃለን" የሚሉ ልሂቃን፥ የሀገርን ችግሮች በመፍታት ስም የሥልጣን ክፍፍል የሚያደርጉባቸው ጉባኤዎች ተካሂደዋል። የዘመናት ጥያቄዎቻችን ግን መፍትሄ አላገኙም። ከልሂቃን ድርድር ይልቅ ሕዝባችን ራሱ መክሮ ራሱ መፍትሔ የሚያመለክትበት ሀገራዊ ምክክር ማድረግ ያስፈለገን በዚህ ምክንያት ነው። በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ታሪክ በደማቅ ብዕር የሚጻፍ ታላቅ ጉባኤም ተከናወነ።

በተካሄደው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ ሕዝባችንን ዋና ባለቤትና ዋና ተዋናይ በማድረግ ተጠናቅቋል። ሁሉንም አካባቢዎች፤ ሁሉንም ብሔረሰቦች፤ ሁሉንም እምነቶች፤ አብዛኞቹን የፖለቲካ አመለካከቶች፤ ሀገር ቤቱንና ዳያስፖራውን፤ ገበሬውን፣ አርብቶ አደሩንና ወዛደሩን፤ የሥራ ኃላፊዎችንና መደበኛ ዜጎችን፤ የተማሩትንና ያልተማሩትን፤ ወንዶችንና ሴቶችን፤ በዚህ መጠን በአንድ ጉባኤ በአንድ ቦታ ማገናኘት አዲስ ታሪካችን ነው። በዘመን መጽሐፍም በወርቅ ቀለም ተጽፏል።

ሦስተኛው "ውጤቱ" ነው። በአጀንዳዎች ላይ ተግባብተናል። እነዚህ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች አንድ በአንድ ወደ ተግባር የሚወሰዱ ናቸው። ባህል የሚሆኑ አሉ። ሥርዓት የሚሆኑ አሉ። አሠራር ተደርገው የሚዘረጉ አሉ። ዕሳቤ ሆነው የምንመራባቸው አሉ። ዐዋጅ ሆነው የሚወጡ አሉ። የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሐሳቦች የሚሆኑ አሉ። የመዋቅር ማሻሻያ የሚሆኑ አሉ። የነገዎችን ትዕምርቶች፣ ሐውልቶች፣ ስያሜዎችና ሀገራዊ ብራንዶች የሚወስኑ አሉ። የትናንት ጉዟችንን የሚያርሙ፣ የሚያስታርቁና በተሻለ መግባባት የሚተረጉሙ አሉ።

መንግሥት ሁሉንም ሐሳቦች በተገቢው መንገድ ይጠቀምባቸዋል። የሀገራዊ ምክክር ውጤቶች የኢትዮጵያን የነገ ጉዞ በሚያቃና መልኩ ግብአት ሆነው ያገለግላሉ። በየጊዜው የሚጠቀሱ፣ የሚወሱና የሚነሡ ዕሳቤዎች ይሆናሉ። የኢትዮጵያ የዘመን መጽሐፍ ከሀገራዊ ምክክሩ በፊትና በኋላ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

የተለየ ነገር እንደሚጽፍ አምናለሁ። የመግባባት፣ የመስማማትና የመሰናኘት ጉዟችን እየሠመረ መሄዱን ይመዘግባል። የተግባባንባቸው ሐሳቦች መሬት ወርደው፣ ሥር ይዘው፣ ፍሬ ማፍራታቸውን ይተርካል።

ሀገራዊ ምክክራችን ገደ መልካም መሆኑን በምክክሩ ብቻ ሳይሆን በውጤቱም እያሳየ ነው። በአዲስ ዓመት ዋዜማ በመቶ የሚቆጠሩ ታራሚዎችን መንግሥት በምሕረት እንዲፈቱ አድርጓል። ይሄንን ያደረገበት ዓላማ ሁለት ነው። የመጀመሪያው የሀገራዊ ምክክሩን ውጤት በፍቅር፣ በይቅርታና በሰላም ለመጀመር ነው። ወደ ሀገራዊ ምክክር የመጡ ልዩ ልዩ ወገኖች በአንድም በሌላም ስሕተት የታሠሩ ወገኖች በይቅርታ እና በህግ አግባብ እንዲፈቱ ጠይቀው ነበር። መንግሥት ይሄንን ተቀብሎ በሂደቱ የተስማሙትን ፈትቷል። የምክክሩም ዓላማ ኢትዮጵያውያን በጉዳዮች ላይ እንዲነጋገሩ የተግባቡባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች እንዲያቀርቡ ነው። መንግሥትም ለምክክሩ ሐሳቦች ትግበራ ያለውን ቁርጠኝነት በዚህ የይቅርታ ሂደት ማሳየት ጀምሯል።

በዚህ የይቅርታ ሂደት የተፈቱ ወገኖች በሀገራዊ ምክክር ምክረ ሐሳቦች ላይ አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይታመናል። ካለፈው መንገድ በመማር የወደፊቱን መንገድ የሰላምና የዴሞክራሲ መንገድ ያደርጉታል ተብሎ ተስፋ ተደርጓል። ማኅበረሰቡም እነዚህ ወገኖች በሀገር ሰላምና ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ማገዝና መምከር አለበት።

መነጋገር፣ መከራከርና መፎካከር ሲቻል ግጭትና ጦርነት አዋጪ አይደለም። የብዕርና የሐሳብ ጊዜ እንጂ የጠመንጃ እና የጉልበት ጊዜ አልፏል። የኢትዮጵያ የዘመን መጽሐፍ ካሁን በኋላ የጠመንጃና የጉልበት ታሪክን አይመዘግብም። በታሪካችን ውስጥ በቂ ግጭቶችና ጦርነቶች መኖራቸውን የዘመን መጽሐፋችን አሳይቶናል። ቀጣዩ ምዕራፍ አዳዲስ መንገዶችን እንጂ አሮጌ አካሄዶችን አይመዘግብም።

ቀጣዩ ዓመት የጉባ ብሥራቶችን የበለጠ ተግባራዊ የምናደርግበት ዘመን ይሆናል፡፡ ዓመቱ የፖለቲካ ምኅዳሩ ሰፍቶ የተለያዩ ዕሳቤዎችንና አካሄዶችን በብሔራዊ ጥቅም አስተሣሥረን የምንጓዝበት ዓመት ይሆናል፡፡ ሁለንተናዊ ሉዓላዊነታችን ይበልጥ የሚከበርበት፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ይበልጥ የሚጸናበት፣ በሁሉም ዘርፎች የጀመርነው ምርታማነት በዓይነትና በጥራት የሚጨምርበት፣ ሀገራችንም የቀጣናውና የአፍሪካ መሪነቷን ሥር መሠረት የምታስይዝበት፤ የኢትዮጵያ ብልጽግና ትውልድ ተሻጋሪ እንዲሆን ተደርጎ የሚገነባበት ዓመት ይሆናል።

ይህ እንዲሳካ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ፣ የልሂቃን ሚና፣ የኃይማኖት አባቶች ጸሎት፣ የጸጥታ ተቋማት ጥንካሬና ቁርጠኝነት፣ የአምራች ኢንዱስትሪው ትጋትና ብርታት፣ የንግዱ ማኅበረሰብ ቅልጥፍናና ለሕዝብ አሳቢነት፣ የገበሬውና የአርሶ አደሩ አይበገሬነት፣ የወጣቶችና ሴቶች ያላሰለሰ ጥረት፣ የሚዲያዎች ሐቀኝነት፣ የዲጂታል ዘርፉ ዘመናዊነት፣ የሲቪል ሰርቫንቱ ንጽሕናና አገልግሎት፣ እጅግ ወሳኞች ናቸው።

አዲሱ ዓመት በኢትዮጵያ የዘመን መጽሐፍ ላይ አዲስ ታሪክ፣ አዲስ ሐሳብና አዲስ ሥልጣኔ የምንጽፍበት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ እንደሚሆንም አምናለሁ። ፈጣሪም እንደሚረዳን እተማመናለሁ።

# "አዲስ... ከገጽ 1 የዞረ

ምርጫ በሰላም ማጠናቀቋንና ታሪካዊውን ብሔራዊ ምክክር በስኬት ማካሄዷን ጠቅሰዋል።

በአዲሱ ዘመን ህዝቡ በድምፁ የመረጠውን መንግስት ለመመስረት፣ የታደሰ ጉልበትና የላቀ ለውጥ ለማምጣት እንዲሁም ታላላቅ የልማት ውጥኖችን ወደ ተግባር ለመለወጥ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ስለሆነም አዲሱ ዓመት ባለፉት ስኬቶች ሳንረካ፣ ጊዜን በከንቱ ሳናባክንና ጉድለቶችን በማረም ለላቀ ውጤት ቃል የምንገባበት ወቅት እንደሆነ አስገንዝበዋል።

ለተመዘገቡት ውጤቶች ምስጢሩ መተባበር፣ መትጋት፣ መከባበርና አብሮነት መሆኑን የገለጹት ከንቲባዋ፣ መጪው ዘመን የበለጠ ያማረ እንዲሆን አብሮነትንና ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን ማጠናከር እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

በመካከላችን ክፍተት ለሚፈልጉ አካላት እድል ሳንሰጥ፣ እጅ ለእጅ ተያይዞ የተጀመረውን የልማት ጉዞ ከዳር ማድረስ ያስፈልጋል።

ጊዜ ጥሎን ሳይሄድ እውቀትና ጉልበትን አስተባብሮ በሀገርና በትውልድ ግንባታ ላይ መተጋገዝ እንደሚገባና ኢትዮጵያ ለሁሉም የሚበቃ ተፈጥሮአዊ ጸጋ ያላት በመሆኗ፣ ለከፋፋይ ትርክቶች ቦታ ሳንሰጥ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን ማጎልበት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ዘመን መለወጫው የብሩህ ተስፋ፣ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን በመመኘት፣ በበዓሉ ወቅት ተፈጥሮ በአበቦች እንደምታጌጥ ሁሉ፣ ኢትዮጵያውያንም በቱባ ባህሎቻቸው በአበባ አየሽ ወይ፣ ሻዳይ፣ አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ሽኖዬና ጎቤ የመሳሰሉ ህብረ-ብሔራዊነትን በሚያደመቁ እሴቶች የሚደምቁበት ወቅት መሆኑን አብራርተዋል።

በመሆኑም አዲሱ ዓመት ከአሮጌው ወደ አዲሱ ዘመን የምንሸጋገርበትና ባህልን የምናደምቅበት ብቻ ሳይሆን፣ ከአንደኛው የለውጥ ምዕራፍ ወደ ሌላ አዲስ የለውጥና የብልጽግና ምዕራፍ የምንሸጋገርበት ታሪካዊ ድልድይ እንደሆነ ገልጸዋል።

## በዓሉን ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለኃይማኖት



ፎቶ- ከገፀ ድር

የቀድሞው የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳትና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊ ጳጳሳት ጉባዔ ፕሬዝዳንት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዝዳንት ቄስ ደረጀ ጀንበሩ

ለአዲስ ዓመት በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለኃይማኖት፣ በሀገራችን በገጠርና በከተማ የምትኖሩ፣ ከሀገር ውጭ በተለያዩ አህጉር የምትገኙ፣ የሀገራችንን ዳር ድንበር ለመጠበቅና ለማስከበር በየጥበቃው የቆማችሁ፣ በሕመም ምክንያት በየጠበሉና በየሆስፒታሉ ያላችሁ፣ እንዲሁም የሕግ ታራሚዎች ሆናችሁ በየማረሚያ ቤቱ የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት በሙሉ እንኳን አደረሳችሁ የሚል የመልካም ምኞት መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ባስተላለፉት የ2019 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓል መልዕክት፣ በየዓመቱ የይቅርታ እጁን እየዘረጋ የሚመግበን እግዚአብሔር አምላካችን እንኳን ከዘመነ ማርቆስ 2018 ዓመተ ምህረት ወደ ዘመነ ሉቃስ 2019 ዓመተ ምህረት በሰላም አደረሰን፣ አደረሳችሁ ብለዋል።

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልጋቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ በማያሻማ ሁኔታ አሳውቋል ያሉት ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ፣ ከእነሱም መካከል በእውነተኛው መንፈስ ንስሐ መግባት፣ መጽናናትና መመለስ ናቸው። የዓለማችን ህዝብ በወሳኝነት ማጽናናት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ ራሳችንን በራሳችን ለማጽናናት እንኳን በቂና ዘላቂ አቅም የሌለን ውስኖች ነን። ይህንን አውቀን እውነቱን፣ የእርሱን እርዳታ እንድንሻ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ይሁንና ከልብ በመጸጸትና ከቀደመው ስህተት ተግባራችን በመመለስ በፊቱ ተንበርክከን መታዘዛችንን በተጨባጭ እንድናሳይ ይፈልጋል የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

እግዚአብሔር ከታላቅ ቸርነቱ የተነሳ የመታደስ ዘመንን በየዓመቱ ከመስጠት አልተቆጠበም። እንደሁልጊዜው አሁንም አዲሱን ዘመን ባርኮ ሰጥቶናል። ሆኖም አዲሱ ዘመን የመጽናናት ዓመት እንዲሆንልን የእኛ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና እንዳለው መዘንጋት የለብንም። ከሁሉ በፊት ያለፈውን ዓመት እንደ ግልም፣ እንደ ማህበረሰብም፣ እንደ ሀገርም፣ እንደ ኃይማኖትም በህሊናችን ልናስበውና ልንገመግመው ይገባል ሲሉም መክረዋል።

ያለፈውን ዓመት በንጹህ ህሊናችን በጥልቀት ስንገመግመው የመጣንበትና ያለፍንበት ስለሆነ ኮለል ብሎ በፊታችን ይታያል። ጥቅሙም ሆነ ጉዳቱ በሙሉ ከእኛ የራቀ ስለማይሆን ዳኝነት ለመስጠትና ውሳኔ ለመወሰን አንቸገርም። በመሆኑም ለፈጸምነው ስህተት ይቅርታን ከመጠየቅ ባሻገር ድጋሚ ላንደግመው መወሰንና ለተግባራዊነቱ በጽናት መቆም አለብን።

እኛ በዚህ ደረጃ ከቀደመው ስህተታችን ተጸጽተን ንስሐ ከገባን እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን አግኝቷል ማለት ነው። በመካከላችንም ትክክለኛ መግባባት ተፈጥሯል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ እርሱ ዘላቂ የሆነ የመጽናናት ዘመን ለእኛ ይሰጠናል።

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን ሁሉ ኢትዮጵያን እንዳለች የጋራ አድርጋችሁ ተቀበሉ። ሌላውን ረጅም ጊዜ ሰጥታችሁ ቢሆንም በውይይትና በመግባባት እየፈታችሁ በአንድነት ቀጥሉ። በይቅርታ መንፈስ በአንድነት ተቃቅፎ ከመቀጠል ውጭ ሌላ የተሻለ እድል እንደሌለ ከልብ ልትገነዘቡ ይገባል ሲሉ ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አባታዊ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በዚህ ሁላችሁም የበኩላችሁን ልባዊ ጥረት ለማድረግ አትቆጠቡ ብለን ከልብ እንመክራለን። በመጨረሻም ለሁሉም መድኃኒቱ ቀና አዕምሮ ነውና በአዲሱ ዓመት እግዚአብሔር ቅንና በጎ አሳቢ አዕምሮን እንዲሰጠን፣ በእሱም ያሉብንን ችግሮች አርመንና አስተካክለን ሰላም የሰፈነበት የመጽናናት ዘመን ማየት እንችል ዘንድ እግዚአብሔር አምላካችንን እንለምናለን።

> “2019 ዓ.ም የተጣሉት የሚታረቁበት፣ ፍቅርና አንድነት የሚጎለብትበት ዓመት እንዲሆን እየተጋን፣ ድሆችንና በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመደገፍ አብሮነታችንንና ፍቅራችንን በተግባር እንድንገልጽ አደራ እንላለን“

የቀድሞው የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳትና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊ ጳጳሳት ጉባዔ ፕሬዝዳንት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል የ2019 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓልን በማስመልከት ያስተላለፉት መልዕክት በአዲሱ ዓመት መባቻ ላይ በመጀመሪያ ለሰማዩ አምላክ ክብርና ምስጋና ማቅረብ ይገባል ብለው፣ ማመስገን አመስጋኙን የሚያሳድግ፣ ትሕትናን የሚገልጽ እና በረከትን የሚያመጣ መንፈሳዊ ተግባር መሆኑን ጠቁመዋል።

ያለፈውን ዓመት በጎ ነገሮች እያሰቡ ማመስገን እንደሚገባ ሁሉ፣ ድክመቶችን እና ስህተቶችን አምኖ ንስሐ መግባት ያስፈልጋል። እውነተኛ ጽድቅ የሚገኘው እንደ ፈሪሳዊው በመታበይ ሳይሆን፣ እንደ ቀራጩ በትሕትና የእግዚአብሔርን ምሕረት በመለመን ነው ሲሉም መክረዋል። በአሁኑ የማህበራዊ ግንኙነት ዘመን በርካታ አፍራሽና በጎ ድምፆች ይሰማሉ ያሉት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ስለሆነም አዲሱን ዓመት ስንቀበል መልካሙንና የሰውን ልጅ ክብር የሚያስጠብቀውን ለመቀበል፣ ጎጂውንና ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበትን ደግሞ ለመሸሽ የሚያስችል የመለየት ፀጋ ከአምላክ መጠየቅ አለብን። ዘመኑ ሰላም፣ ዕርቅና የእግዚአብሔር ፍቅር የሚገዛበት እንዲሆን ተስፋ በማድረግ ሕይወታችንን በአዲስ መንፈስ መምራት ይኖርብናል ብለዋል።

እንደ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ፣ እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ዘመን በጥበብ የመቅረፅና የሰው ልጅ ክብር የሚጠበቅበት፣ ፍትሕና ወንድማማችነት የሚሰፍንበት ማህበረሰብ የመገንባት ኃላፊነት አለበት። የሰው ልጅ ሰብዓዊነቱ በሚጎድልበትና እውነተኛ ማንነቱ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ሁሉ፣ እውነትና ሕይወት ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ቃል በማየትና ዕርስ በዕርስ በመደጋገፍ ወደ ሙሉ ሰብዓዊነት ማደግ ያስፈልጋል።

አዲሱ ዓመት ሀገራችን ከዕርስ በዕርስ ጦርነት የምትወጣበት፣ ስደትና መፈናቀል የሚያበቃበት እንዲሁም የተጣሉ የሚታረቁበት የሰላም ዘመን እንዲሆን አጥብቆ መጸለይ ይገባል። በዓሉን ስናከብርም በችግር፣ በሕመም፣ በእስራትና በጭንቀት ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመጎብኘት፣ ችግራቸውን በማቃለልና ፍቅርን በማጋራት ክርስቲያናዊ ተግባራችንን መወጣት እንዳለብን ጥሪ አስተላልፏል።

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዝዳንት ቄስ ደረጀ ጀንበሩ በበኩላቸው፣ በአምላክ ምህረትና እረኝነት ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ በመሸጋገራችን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንኳን አደረሳችሁ የሚል መልካም ምኞት አስተላልፈዋል።

አክለውም፣ 2018 ዓ.ም የስኬትና የፈተናዎች ዓመት የነበረ ቢሆንም፣ በተለይም ሀገራዊ ምርጫውና የምክክር ጉባኤው በሰላም በመጠናቀቃቸው እንዲሁም የተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶች በመጠናቀቃቸው ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ ይገባል ብለዋል።

በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች በነበሩ ግጭቶች የሰው ሕይወት ማለፉ፣ ወገኖች ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውና ሙሉ ሰላም አለመስፈኑ የደስታችን ማደናቀፊያ ሆኗል። ሆኖም የሀገራችን ሉዓላዊነት ተጠብቆ ለዚህ አዲስ ዓመት በመብቃታችን አምላክን እያመሰገንን፣ ከአዲሱ ዓመት አዲስ እድልና ከትናንት ስህተቶች በመማር ለህዝብና ለሀገር የሚጠቅሙ በጎ ነገሮችን ለማከናወን መዘጋጀት አለብን የሚል ጥሪ አስተላልፈዋል።

ለሀገራችን ሰላምና እድገት ብቸኛው መፍትሔ አንድነታችንን የሚጎዱ ተግባራትን ማስወገድ ነው። አንዳችን ለሌላችን አስፈላጊ መሆናችንን ተረድተን፣ በመመካከርና አንድነታችንን በማጠናከር የሀገራችንን እድገት ማፋጠን ይገባናል። ሀገራችን የተፈጥሮ ሀብትና የሰራተኛ ወጣት ኃይል እያላት ከድህነት አለመውጣቷ የሚያሳዝን በመሆኑ፣ በአዲሱ ዓመት በጥበብና በትጋት በመስራት ድህነትን ታሪክ ልናደርግ ይገባል።

አዲሱን ዓመት በአዲስ አስተሳሰብና በንጹህ ልቦና በመቀበል፣ ንግግራችን፣ መዝሙራችንና ጩኸታችን ሁሉ ስለ ሰላም ብቻ ሊሆን ይገባል። በፍጹም መከባበርና መደማመጥ ስለ ጋራ ሰላማችን ልንመክር ይገባል። ይህ ከሆነ ያለፉት አስጨናቂ ጊዜያት አልፈው፣ አስተማማኝ ሰላም የነገሰባትና ሁላችንም የምንኮራባት ኢትዮጵያን የምናይበት ብሩህ ዘመን ቅርብ ይሆናል።

2019 ዓ.ም የተጣሉት የሚታረቁበት፣ ፍቅርና አንድነት የሚጎለብትበት ዓመት እንዲሆን እየተጋን፣ ድሆችንና በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመደገፍ አብሮነታችንንና ፍቅራችንን በተግባር እንድንገልጽ አደራ እንላለን የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

# እንኳን አደረሳችሁ!

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
Addis Ababa City Administration

የሁላችን ከተማ አዲስ አበባ እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ ትላለች። ከተማችን አዲስ አበባ ገፅታዋን እየለወጠች፣ የምትጀምራቸውን ፕሮጀክቶች በፍጥነትና በጥራት እያጠናቀቀች ነዋሪዎቿን እያቀፈች፣ መስህቦቿን እያበዛች፣ በፍጥነት እየተራመደች ትገኛለች። ለዘመናት የተጫናትን እርጅና የገፈፈችው አዲስ አበባ ውብ የቱሪስት መዳረሻዎችን በማስፋት ለዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ኩነቶች ተመራጭ፣ ንፁህ፣ አረንጓዴ ውብ ሥፍራን የተላበሰች፣ አሰራሯን ያዘመነች፣ ህብረ ብሔራዊነቷን የጠበቀችና ሰላሟ የተረጋገጠ ውብ ከተማ መሆን ችላለች። በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት በሰው ተኮር ስራዎቿ የነዋሪዎቿን እንባ ያበሰች፣ መደገፊያ መጠጊያ የሆነች፣ ተስፋን የሰጠች የተጣሉትን ያስታወሰች፣ የተራቡትን ያጎረሰች፣ ህፃናቷን የደገፈች፣ ተማሪዎቿን ያስታወሰች፣ ማዕድ ያጋራች፣ የኑሮን ጫና ለማቅለል ሸክምን የተጋራች፣ ሌማት እንዲሞላ ያገዘች፤ እንደ አዲስ የተፈጠረች ከተማ ሆናለች። ለነገ ትውልድ የሚተርፍ ስንቅ ሰንቃ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለጎብኚዎቿ ሳቢ የሆነችው መዲናችን አዲስ አበባ፣ እንደ ስሟ አዲስ ውብ አበባ ሆና እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሳችሁ ትላለች።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጪው ዘመን ከተማችን አዲስ አበባ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ዘርፍ የላቀ ስኬት የምታስመዘግብበት የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነትና ይበልጥ ትጋት የምንጎናፀፍበት እንዲሆን መልካም ምኞቱን ያስተላልፋል።

**መልካም አዲስ ዓመት!!**

**2019**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መልካም በዓል!



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
CLEANING MANAGMENT AGENCY
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

በየቤታችንና በተቋሞቻችን የምናመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ካልተያዘ ለአካባቢ ንጽህና ጉድለት፣ ለተላላፊ በሽታዎች መዛመት እና ለከተማችን ውበት መጓደል ከፍተኛ ስጋት ይሆናል። ስለዚህ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች በመታገዝ የፕላስቲክ፣ የወረቀት እና የምግብ ተረፈ ምርቶችን የመለየትና በየእቃው የማስቀመጥ ልምድ ልናዳብር ይገባል። ይህም የአዲስ ሀብት፣ የስራ እድል እና የኢኮኖሚ ልማት ምንጭ ነው። ስለዚህ ቆሻሻን እንደ እምቅ ሃብት በመመልከት ስልታዊ አሰራር መዘርጋት ለከተማችን የነገ ዕድገት ወሳኝ ሚና መጫወት አለብን።
ቆሻሻን ከምንጩ ለይቶ ማስቀመጥ አካባቢያችንን ያጸዳል፤ ለብዙዎች የስራ እድል ይፈጥራል፤ የከተማችንንም ፅዳት ያረጋግጣል።

ዛሬውኑ ከራሳችን እንጀምር!

ፅዳትን ባህል እናድርግ!

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ!

**2019**

## እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ አደረሰን!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን በከተማችን የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስሉጡ፣ ግልፅና ፍትሃዊ እንዲሆን በማድረግ ከተማችን ከዓመት ዓመት ውብና ጽዱ ሆና ተምሳሌት የአፍሪካ ከተማ ከማድረግ ባሻገር በርካታ ዘርፈ ብዙ ማዘጋጃ ቤታዊ ስራዎችን በመስራት ስኬታማ ዓመትን ማሳለፍ ችሏል! ቆሻሻን ከማጽዳት ባሻገር ወደ ሀብትነት ከመቀየር አንፃር ተግቶ ሰርቷል። የመብራት አገልግሎትን ከማዳረስና ከተማችን ሁሌም በስራ ላይ እንድትሆን መንገዶች በብርሃን አሽብርቀው እንዲታዩ ከማድረግ በላይ አስተማማኝ በማድረግ፣ አደጋን ከመከላከል ባለፈ የአደጋ ስጋት እንዲቀንስና ለኑሮ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ዲጂታል አዲስ አበባን በመገንባት አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው እንዲሰጡና ስማርት ሲቲን መፍጠር በቁ የመሰረተ ልማት ትስስር የተረጋገጠባት ከተማ ሆና እንድትቀጥል በርካታ ዘርፈ ብዙ ስኬቶችን በመከወን እንደስሟ አዲስ አበባን አዲስ የማድረግ ስራን በላቀ ደረጃ መከወን ችሏል።

በቀጣይ በ2019 አዲስ ዓመትም እነዚህን አፈጻጸሞች በላቀ ደረጃ በመፈፀም አዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ረገድ የስማርት ሲቲ ከተማ ስታንዳርድ የምታሟላ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹና ለቱሪስቶች ተመራጭ እንድትሆን ተጠሪ ተቋማቱን፣ ባለድርሻ አካላትንና የከተማዋን ነዋሪ በማሳተፍ የላቀ ውጤትና ስኬት ለማስመዝገብ ጠንክሮ የሚሰራ መሆኑን ያሳውቃል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት

2019

መልካም አዲስ ዓመት!!



# በተስፋ የታጀበው የዘመን ሽግግር

**በጊዜው አማረ**

2018 ዓ.ም ተጠናቅቆ፣ አሮጌ ዓመት ተብሏል፤ ኢትዮጵያዊያንም 2019 ዓ.ምን ተቀብለዋል፡፡ አዲሱ ዓመት የስራ፣ የሰላምና የስኬት ዓመት እንደሚሆንም ተስፋ ሰንቀዋል፡፡ ኢትዮጵያ በ2018 ዓ.ም ካከናወነቻቸው ዋና ዋና እና ታሪካዊ ተግባራት መካከል ሀገራዊ ምክክሩ አንዱ ነው። ይህ መድረክ በሀገሪቱ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ታሪክ ውስጥ ለዘመናት የዘለቁ ልዩነቶችን፣ አለመግባባቶችን እና የታሪክ ክፍተቶችን በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት የተወጠነ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት ነው። ህዝቡ በየደረጃው በነፃነት ሀሳቡን እንዲገልጽ እና ለሀገር ሰላም እንዲሁም አንድነት መፍትሄ እንዲያመላክት ያደረገ ትልቅ እርምጃ ሆኖም ተመዝግቧል።

ይህ በ2018 ዓ.ም የተከናወነው የምክክር ሂደት በዋናነት ያተኮረው በህዝብ ተሳትፎ እና አካታችነት ላይ ነበር። ፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የማህበረሰብ መሪዎችን፣ የኃይማኖት አባቶችን፣ የሲቪል ማህበራትን ጨምሮ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ተወካዮች በአንድ መድረክ ተገናኝተው በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የመከሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ዓይነቱ አካታች አሰራር ዜጎች በሀገራቸው የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ቀጥተኛ ባለቤትነት እንዲሰማቸው ከማድረጉም በላይ፣ በውይይት ማመንን ብቸኛ የፖለቲካ ባህል ለማድረግ ትልቅ መንገድ ከፍቷል።

በምክክሩ ወቅት የተነሱት አጀንዳዎች የሀገሪቱን ዘላቂ ሰላም፣ ሕገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎችን፣ የፍትህ እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን እንዲሁም የጋራ ሀገራዊ ትርክት መገንባትን ያካተቱ ነበሩ። በታሪክ እና በፖለቲካ አመለካከት ምክንያት የተራራቁ የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራ ጠረጴዛ ዙሪያ በመቀመጥ እርስ በእርስ ለመደማመጥ እና የችግሮችን መነሻ በጋራ ለመረዳት ያደረጉት ጥረት በሀገሪቱ የሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ይህም ለዓመታት የዘለቁ ቅሬታዎችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል እንዲጎለብት አስችሏል።

ይህ አዲስ ምዕራፍ ወይዘሮ አዜብ ተክለሃይማኖትን ጨምሮ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እናቶች፣ አባቶች እና ወጣቶች በአዲሱ ዓመት በውስጣቸው ብሩህ ተስፋና አዲስ መንፈስ እንዲሰንቁ አድርጓቸዋል። ላለፉት ዓመታት በሀገሪቱ የነበሩት አለመግባባቶችና አለመረጋጋቶች የማህበረሰቡን ዕለታዊ ህይወትና የስነ-ልቦና እረፍት ፈትነው የቆዩ ቢሆንም፣ በ2018 ዓ.ም የተከናወኑት የሰላምና የምክክር አበይት ተግባራት ህዝቡ ነገን በተሻለ እይታ እንዲመለከት ትልቅ ስነ-ልቦናዊ ስንቅ ሆኖታል።

ወይዘሮ አዜብ ለዝግጅት ክፍላችን




ፎቶ ፦ ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
ምክክሩ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ብልፅግናን ለማረጋገጥ አቅም የሚፈጥር ነው

በሰጡት አስተያየት፣ “ዘንድሮ ልጄ 12ኛ ክፍል ተፈትና አልፋለች፡፡ በአዲሱ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ትገባለች፡፡ እናም በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ ልጄ በፈለገችው ዩኒቨርሲቲ ሄዳ መማር የምትችልበት እድል እንደሚፈጠር ተስፋ አደርጋለሁ” ብለዋል፡፡

ወይዘሮ አዜብን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን አዲሱን ዓመት በተስፋ የተቀበሉት የጋራ ውይይትና የመከባበር ባህል መጎልበት ለቀጣዩ ትውልድ የተረጋጋችና የበለፀገች ሀገርን ለማስረከብ ያስችላል ከሚል ፅኑ እምነት በመነሳት ነው። በሀገራዊ ምክክሩ ወቅት የታዩት አካታች መድረኮች እና የዜጎች የመደማመጥ ሁኔታ፣ የማህበረሰቡ አባላት በሀገራቸው የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ያላቸውን አመኔታ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮታል።

በሹፌርነት ሙያ ቤተሰቡን የሚያስተዳድረው ወጣት አበበ ጥላሁንም፣ “የምክክሩ ምክረ ሃሳብ ሲተገበር ሀገራችን ሰላም ትሆናለች። አዲሱ ዓመትም እንደ ልብ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰን የምንሰራበት ይሆናል ብዬ አስባለሁ” ሲል የወይዘሮ አዜብን ሀሳብ አጠናክሯል፡፡

በ2018 ዓ.ም እና ከዚያም በፊት የተዘሩት የሰላምና የመግባባት ዘሮች በአዲሱ ዓመት አፍርተው ዘላቂ ፍቅርን፣ አንድነትንና ልማትን ያመጣሉ የሚል ተስፋ በየቤተሰቡ ዘንድ ጎልቶ ይታያል። ይህም ኢትዮጵያውያን በአዲሱ ዓመት ለሀገራቸው ዘላቂ ሰላምና ዕድገት በጋራ እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን አዲስ ጉልበትና ተስፋ ፈጥሮላቸዋል።

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ተንታኙ አቶ ዳያሞ ዳሌ በሀገራዊ ምክክሩ ከአጀንዳ መረጣ እስከ ተሳታፊ ልየታ ድረስ በነበሩ አበይት ሂደቶች ውስጥ የላቀ ተሳትፎ አድርገዋል። በሲዳማ ክልል ደረጃ በተካሄደው የአጀንዳ መረጣ መድረክ እና በአዲስ አበባ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው አጠቃላይ ምክክር ላይም ተሳትፈዋል፡፡

ይህን ምክክር እንደ ወርቃማ ታሪካዊ ምዕራፍ እንደሚያዩት የገለጹት ዳያሞ፣ የተራራቀ አጀንዳና ፍላጎት ያላቸው ወገኖች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ስለ ሀገር የተወያዩበት መሆኑን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አብራርተዋል።

የዚህ አይነት የምክክር ሂደት የህዝብን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ባለፈ በፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ የህብረተሰቡን እውነተኛ ድምጽ ለማንጸባረቅ ከፍተኛ ሚና አለው። በምክክሩ ወቅት የተሰጡት የባለሙያ ትንታኔዎች፣ ከመላው ሀገሪቱ የተሰሙ ድምጾች ለቀጣይ የኢትዮጵያ ሰላም፣ ልማትና እድገት ጠንካራ መሰረት የሚጥሉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በእርግጥም የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ያካሄደው የምክክር መድረክ የሀገሪቱን የወደፊት ጉዞ ብሩህ የሚያደርግ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። አቶ ዳያሞ እንደገለጹት፣ በምክክሩ ላይ የተሳተፉት ተመካካሪዎች ያሳዩት ከፍተኛ የነቃ ተሳትፎና ያቀረቧቸው በሳል የምክረ ሃሳብ ነጥቦች የኢትዮጵያዊያንን ጥልቅ አርቆ አሳቢነት የሚያሳዩ ናቸው። መድረኩ በግልጽነትና በከፍተኛ የስነ-ምግባር ጨዋታ የተከናወነ በመሆኑ፣ የህዝቡን የጋራ እይታና የመፍትሔ ሀሳቦች ወደፊት ለማምጣት ትልቅ መሰረት ጥሏል።

ይህ በምክክሩ ወቅት የታየው

> **ወደ 2019 ዓ.ም የተደረገው ሽግግር የዓመት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የዜጎች ስነ-ልቦና እና የሀገር አቅጣጫ የታደሰበት ታሪካዊ አጋጣሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን የገጠሟቸውን ፈተናዎች በውይይት የመሻገር አቅማቸውን ያስመሰከሩበት ወቅት ነው**

የሰለጠነ አካሄድ ኢትዮጵያዊያን ያሉባቸውን ልዩነቶች በጦርነትና በግጭት ሳይሆን በሰላማዊ ውይይት መፍታት የሚችሉ ህዝቦች መሆናቸውን ለመላው ዓለም ያስመሰከረ አጋጣሚ ሆኗል። ለዘመናት የቆዩ አመለካከቶችንና አለመግባባቶችን በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ በመቀመጥ ለመፍታት የተደረገው ጥረት የህዝቡን ድንቅ ባህልና የመቻቻል እሴት አጉልቶ አሳይቷል። ይህም የሃይል እርምጃ አሸናፊ እንደሌለውና ብቸኛው ዘላቂ መፍትሔ ውይይት መሆኑን ያረጋገጠ ነው።

ይህ መድረክ በሀገራችን የፖለቲካና የማህበራዊ ታሪክ ውስጥ አዲስ ተስፋ፣ አዲስ ልምምድና አዲስ ታሪክ ይዞ የመጣ ክስተት ነው። ግጭቶችን በውይይት የመፍታት ባህል ማዳበር ለአንድ ሀገር እድገትና ዘላቂ ሰላም ወሳኝ በመሆኑ፣ ይህ እርምጃ ወደፊት ለሚደረጉ መሰል ሀገራዊ ጉዳዮች ትልቅ አቅጣጫ ጠቋሚ ይሆናል። የውይይትና የምክክር ባህሉ እየዳበረ ሲሄድ የህግ የበላይነትና የህዝቦች አብሮነት የበለጠ እየጎለበተ ይሄዳል ይላሉ፤ ምሁሩ ዳያሞ ዳሌ።

በተለይም የምክክር መድረኩ የተከናወነው በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ መሆኑ ልዩ ትርጉም ተሰጥቶታል። 2019 ዓ.ም የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት እንዲሆን ተስፋ ሰጪ ስራዎች በዚሁ ምክክር ላይ ታይተዋል። በመሆኑም ይህ በዋዜማው የታየው የሰላምና የውይይት ተስፋ በአዲሱ ዓመት አብቦ ለሀገራችን ዘላቂ ሰላምና እውነተኛ አንድነት ፍሬ እንደሚያፈራ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል። ዳያሞ ዳሌም ሆኑ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪዎች በዚህ ሙሉ እምነት እንዳላቸው ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ አስረድተዋል፡፡

የፖለቲካና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ተንታኙ ዳያሞ፣ የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ በራሱ ሙሉ በሙሉ ሁሉንም ችግሮች በአንድ ጀምበር ባይፈታም፣ ለዘላቂ ብሔራዊ መግባባት እና ለጠንካራ ሀገረ-መንግስት ግንባታ መሰረት ይጥላል። የውይይቱን ውጤቶች እና የተደረሱ ስምምነቶችን ወደ ተግባር በመቀየር ረገድ የሚሰሩ ስራዎች የኢትዮጵያን የወደፊት የሰላም እና የእድገት ጉዞ አቅጣጫ የሚወስኑ ይሆናሉ በማለት አብራርተዋል።

ይህ በተስፋ የተሞላ ሽግግር በዜጎች ዘንድ አዲስ ጉልበትና መነቃቃትን በመፍጠር፣ ሁሉም በአዲሱ ዓመት ለጋራ በጎ ዓላማ እንዲነሳሳ መንገድ ይከፍታል። ባለፉት ዓመታት የተዘሩት የሰላምና የመግባባት ዘሮች በ2019 ዓ.ም አፍርተው ለሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ወንድማማችነትና እህትማማችነት መሰረት እንደሚሆኑ

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

# አዲስ አበባ እና አዲስ ዓመት

**በመለሰ ተሰጋ**

አዲስ ዓመት የአዲስ ቀን መግቢያ ብቻ አይደለም፤ የአዲስ ምኞት፣ የአዲስ ጉጉትና የአዲስ ተስፋ መነሻ ጭምር እንጂ። የትናንቱን በትዝታ አስቀምጦ፣ የነገውን በተስፋ ከፍቶ የሚመጣ አዲስ ገጽ ነው። እናም አዲስ ዓመት ሰውን በተስፋ እንደሚያድስ፣ አዲስ አበባም በሚያስደንቅ ለውጥ እንደ ንስር ራሷን እያደሰች ነው።



ፎቶ፡- ከገፀ ድር

አዲስ አበባን ውብ ገፅታ ካላበሱ የልማት ስራዎች መካከል አንዱ የሆነው የአራዳ ፓርክ በከፊል

አዲስ አበባ የትናንት ጎስቋላ ገፅታዋን በአዲስ እሳቤ ገፍፋ፣ በተለያዩ ቀለማት አሸብርቃ፣ በጠቢባን እጆች የተቋጩ እና ከተፈጥሮ ጋር የተወዳጁ ውብና ፅዱ መንገዶቿን በዘርፋፋ ቀሚሷ ላይ እንደ ነጠላ አጣፍታ፣ ዘለግ ብለው እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቁ የመንገድ ዳር የመብራት ምሰሶዎችን እንደ በትረ ሙሴ በኩራት ጨብጣ፣ የቀበና እና ባንተይቀጡ ወንዞችን እንደ ውድ የጆሮ ጌጥ በቀኝና በግራዋ ሰክታ፣ በመልክ በረድፉ ፀጉሮቿን ጎንጉና፣ በቀጭኑ በተኳሉት ዓይኖቿ ሁሉንም በእኩል ስትመለከት እንደ እኔ ላስተዋላት የቱሪዝሟ እመቤት ውቢት አመንሲሳን በቅጽል ስሟ ውቢት ኢትዮጵያን አሊያም የሙዚቃ ፈርጡ፡-

ጥላሁን ገሰሰ "ቃላቶች ያጥሩኛል ማን ብዬ ልጥራሽ፤

እንዲያው በደፈናው ሞናሊዛዬነሽ" ሲል ያዜመላትን ውብና ሽቅርቅሯን የሊዮናርዶ ዳ ቪንቺን የጥበብ እመቤትን ትመስላለች።

በነገራችን ላይ ሞናሊዛ በአንድ ጀንበር አልተሳለችም፡፡ አዲስ አበባም በኢትዮጵያውያን የጥበብ እጆች በዘመን ሰሌዳ የተሳለች አፍሪካዊ እመቤት ናት። ታሪክ እንደሚነግረን ሊዮናርዶ ሞናሊዛን በአርበ ልቦናው ላይ መቼ እንደሳላት ማወቅ ባይቻልም ብሩሹን አንስቶ የልቡን እመቤት ሸራ ላይ ማስቀመጥ የጀመረው ግን እ.ኤ.አ በ1503 አካባቢ በጣሊያኗ ፍሎረንስ ከተማ ነበር፡፡

አሜሪካዊው የግለ ታሪክ ጸሐፊ፣ ጋዜጠኛ እና የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ዋልተር አይዛክሰን፣ በሊዮናርዶ ማስታወሻ ደብተሮች ላይ ተመስርቶ እ.ኤ.አ 2007 "Leonardo da Vinci" በሚል ርዕስ ባሰናዳው መጽሐፉ ከራሱ ታርቆ ወደ ውስጡ ጠልቆ ደግሞም ወደ ውጪ ከቅርብ እስከ አድማስ ተፈጥሮን መርምሮ ሞናሊዛ ማማሯ መድመቋ ከአካባቢዋ ጋር አብሮ እንዲወዳጅ፣ ፈገግታዋ ባያት ሁሉ ግርምትና ደስታን እንዲዘራ ከሰባት ዓመታት በላይ ጊዜ ፈጅቶ እየደጋገመ የኳላት የጥበብ እመቤት መሆኗን ያትታል።

አዲስ አበባም ልክ እንደ ሞናሊዛ በጠቢባን እጆች ደጋግማ የተሳለች የከተሞች ንግሥት ናት። እኔም በዚህ ውበቷ እየተደመምኩኝ ከሰባ ደረጃ ብዙም ሳልርቅ፣ አራዳ ፓርክ መዳረሻ ራስ መኮንን ድልድይ ግድም በአንደኛው ጥግ አረፍ ብያለሁ። በዘመን መግፋት የወየቡ የአዲስ አበባን የትናንት ገፆች በትዝታ እየገለጥኩ፣ የዛሬ ፈገግታዋን በእውነት መነፅር እየተመለከትኩ፣ እንደ አዲስ ዓመት አይቀሬ የሆነውን የከፍታ ዘመኗን እያማተርኩ በልቤ ሰሌዳ የፃፍኩትን እውነት አነብላችኋለሁ፡፡

አዲስ አበባ በዘመን መግፋት ያደፈ ሸማዋን ጥላ በሀገር ልጆች የተሰራ፣ ከራስ የተስማማ፣ ከዘመን የታረቀ ፀአዳ ልብስን ተጎናፅፋለች፡፡ የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገዶቿ በአረንጓዴ እፀዋት ታጅበዋል። በየአቅጣጫው ብቅ ብቅ የሚሉ አበቦች ቀለማቸው በዓይን ይገባል፤ ውበታቸው ደግሞ ወደ ልብ ይወርዳል። አበቦቹ ውብ መንገዶቿን እንደ ብሩሽ ተጠቅመው ልክ እንደ ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ አሊያም እንደ ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ አዲስ አበባን በምልዐት ይስሉታል። አዲስ ዓመት በተፈጥሮ እንደሚያጌጥ አዲስ አበባም እንዲሁ ትዋባለች፡፡

እዚህ አረፍ ባልኩበት አካባቢ ሽር ብትን ከሚለው ወፈ ሰማይ መካከል አንዳንዱ በከተማዋ ውበት እየተሸነፈ ከራሱ ጋር ታርቆ ከተፈጥሮ ወደተወዳጀው አራዳ ፓርክ ጎራ ይላል። ይህንን የመሳሰሉ የከተማዋ ውብ ስፍራዎች ፀሐይን ቀን ብቻ ሳይሆን ማታም የምትወጣ ያስመስሏታል። የከተማዋ የመንገድ ዳር መብራቶች ሌሊቱን በብርሃን ይገልጡታል። ትናንት የእርጅና ሸክም የተጫናቸው የሚመስሉ ቦታዎች ዛሬ የወጣትነት ጉልበትን የተላበሱ ይመስላሉ። የመዲናዋ ሌሊትም ከጨለማ ይልቅ ብርሃንን የሚወድድ እየሆነ ስለመምጣቱ ብዙዎቻችን ምስክር ነን፡፡

ቀበናና ባንተይቀጡን የመሳሰሉ የመዲናዋ ወንዞች ትናንት የተዘነጉ የከተማ ጠርዞች ይመስሉ ነበር። ዛሬ ግን እንደ ንስር ክንፋቸውን ዘርግተው፣ ከአሮጌው ገጽታ ተላቅቀው፣ የከተማዋን ውበት እንደ ውድ ጌጥ እያደመቁት ነው። ይህም የወንዝ ዳር ልማት ማለት ውሃን ብቻ መንከባከብ አለመሆኑን የሚመሰክር ህያው ሐውልት ነው፡፡

አዎ፣ አዲስ ዓመት እንደ አዲስ ገጽ ነው፤ አዲስ አበባም እንደ አዲስ መጽሐፍ ገጾቿን እየቀያየረች ነው። የትናንቱ የተጎሳቆለ ገጽ በዛሬው የልማት ቀለም እየተሸፈነ ነው። የትናንቱ የተዘነጋ ወንዝ ዛሬ የከተማ ውበት ማሳያ እየሆነ ነው።

ታዲያ አዲስ አበባና አዲስ ዓመት ምን ያገናኛቸዋል? ቢሉ አዲስ ዓመት በዘመን ላይ የሚመጣ አዲስ ጅማሬ ነው፤ አሮጌውን ሽሮ አዲስ ጉልበት፣ አዲስ እውነት፣ አዲስ ውበት ይዞ ነገር ግን ባለው ላይ ጨምሮ የሚታይ ነው። አዲስ አበባም የትናንት ወግና ለዛዋን ጠብቃ ግን ደግሞ ከስሟ ያልገጠመውን እርጅናዋን እንደ ንስር አድሳ፣ አዲስ ውበትን ተጎናፅፋ ከአዲሱ ዓመት ጋር አዲስ ሆና ትታያለች።

የአዲስ አበባን ትናንትና ዛሬ ፍንትው አድርገው ከሚያሳዩ ህያው ቅርሶች መካከል እኔ ያለሁበት ይህ የራስ መኮንን ድልድይ አንዱ ነው። ራስ መኮንን ድልድይ ከአዲስ አበባ ቀደምት የመሠረተ ልማት ሥራዎች ጋር የሚያያዝ በአደባባይ የተገለጠ የታሪክ መዝገብ ነው። ዛሬ ደግሞ በኮሪደር ልማት አዲስ ውበትን እና ብርቱ ጉልበትን ተጎናፅፎ ትናንትና ዛሬ ተስማምተው ታሪክን የሚያሳዩበት መንገድም መስታወትም ሆኗል፡፡

አዎ! አዲስ አበባ በየዘመኑ ራሷን ከፍ እያደረገች እንደ አዲስ የምትወለድ ከተማ ናት። ትናንትን በልቧ አቅፋ፣ ዛሬን በእጇ ይዛ፣ ነገን በዓይኗ እያየች በለውጥ ምዕራፍ ላይ ናት። በዚህ የዘመናት ጉዞዋ መካከልም አራዳ ፓርክን የመሳሰሉ ስፍራዎች የተፈጥሮና የሰው ልጅ በምናብ የሚገናኙባቸው፣ ማህበራዊ ሕይወት የሚጎለብትባቸው እና ትውልድ በሙሉ ስብዕና የሚገነባባቸው ሆነው በኮሪደር ልማት ተወልደዋል።

እስኪ ደግሞ ከራስ መኮንን ድልድይ ወደ ዓድዋ ሙዚየም ከፍ እንበል፡፡ አሁን ፒያሳ ደርሰናል፡፡ ይህች ፒያሳ፣ እንደ ከረመ ወይን እያደር የምትጣፍጥ፣ ዙሪያዋን ወዝና ለዛ ባላቸው አካባቢዎች ተከብባ መሃሏ ገነት የሆነች ተናፋቂ የአዲስ አበባ ማዕከላዊ ስፍራ ናት። ጋሽ ስብሐት ገ/እግዚሐብሔር 'ትኩሳት' ብሎ በጠራው መጽሐፉ ጀርባ ላይ እንዳለው የትናንቷ ፒያሳ ዛሬ እንደ ንስር ታድሳለች። አሊያም የብዙዎች ትዝታ ወደሆነው ሰባ ደረጃ ወረድ ብለው የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህንን መታሰቢያ ሐውልት ስር በመንፈስ አረፍ ብሎ የታሪክ ድርሳናትን እየገለጡ መረዳት ይቻላል።

ዛሬ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ዞር ዞር ስንል፣ ከጫጫታው እና ከወከባው ገለል የምንልባቸው ፈዋሽ ታሪኮችን እና ዕውነታዎችን የምንሸምትባቸው አያሌ ስፍራዎች ተገንብተዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የእንጦጦ ፓርክን ተከትለን እስከ ቀበና ወንዝ ድረስ ያለውን ስፍራ መመልከት በቂ ነው፡፡ ከእንጦጦ ተራራ ወደ ሽሮ ሜዳ ወረድ ካሉ ደግሞ በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ቀለማት ያሸበረቁ የባህል አልባሳትን ተመልክተው ዘና ይላሉ።

ወደ አራት ኪሎ ዝቅ ስንል ደግሞ የአብርሆት ቤተ መጻሕፍትን እናገኛለን። በህንፃው ደጃፍ የቆመው ኪነ ሐውልት የልጅነትን ነፃነት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ዓለምና እውነትን የመረዳትን ጉዞ የሚመሰክር ግሩም ጥበብ ነው። ወደ ውስጥ ከገቡ ደግሞ የእውቀት ማዕድ በመልክ በረድፉ ተዘጋጅቶ ይጠብቅዎታል፤ እዚህ ስፍራ ልክ እንደ አዲስ ዓመት አዲስ ሕይወት አለ፡፡

በእርግጥም ከፒያሳ እስከ ቦሌ፣ ከመገናኛ እስከ ሲኤምሲ፣ ከአስኮ እስከ ሜክሲኮ፣ ከአንዱ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ ሲያሻዎት በተዋበው ጎዳና በእግር፣ ከፈለጉም በሰፋፊዎቹ የተሽከርካሪ መንገዶች ሲንቀሳቀሱ ከልብ ካስተዋሉ አዲስ አበባ እንደ አዲስ ዓመት ተስፋን፣ ፍቅርን እና በረከትን ተጎናፅፋ ትታይዎታለች፡፡

> **አዲስ አበባ እንደ አዲስ ዓመት አሮጌውንና የተጎሳቆለውን ገጽታዋን በልማት፣ በውበትና በብርሃን በመተካት ራሷን እንደ ንስር የምታድስ የተስፋና የከፍታ ከተማ ናት**

# በከተማ ልማት የፈካ ህይወት

**• ከደረጃ በታች የነበሩ ቤቶችን አፍርሶ በዘመናዊ ሕንፃዎች መተካት ሰብዓዊ ክብርንና ማኅበራዊ ፍትሕን ያረጋገጠ ልማት መሆኑ ተጠቁሟል**



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
በልደታ ክፍለ ከተማ መልሶ ማልማት ተግባር በተገነባው 'የበጎነት መኖሪያ መንደር' ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ አበባ ካሳ



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
በልደታ ክፍለ ከተማ መልሶ ማልማት ተግባር በተገነባው 'የበጎነት መኖሪያ መንደር' ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ዙፋን

**በቶለሳ መብራቴ**

ወይዘሮ ዙፋን ስጦታው በልደታ ክፍለ ከተማ በአሁኑ ስያሜ የበጎነት መኖሪያ መንደር ነዋሪ ናቸው፤ ለ65 ዓመታት ያህል በኖሩበት አሮጌው የቀበሌ ቤት ውስጥ ያሳለፉት ሕይወት በስጋትና በጭንቀት የተሞላ እንደነበር ያስታውሳሉ። በዚያ የጭቃ ቤት ውስጥ እያንዳንዱ የክረምት ወራት ሲመጣ ደስታን ሳይሆን ፍርሃትን ይዞ ይመጣ ነበር። የቤቱ አፈር እየረገፈ፣ ጣሪያው እያፈሰሰ እና ከቤታቸው ሥር ያለው ገደል የመናድ አደጋ እያንዣበበበት እንቅልፍ አጥተው ከልጆቻቸው ጋር የሚያድሩበት ጊዜ የሚረሳ አይደለም ይላሉ።

በአካባቢው በርካታ ነዋሪዎች የሚጠቀሙበት አንድ የጋራ መፀዳጃ ቤትና የበዛ የኑሮ እንግልት፣ የጤና እክል ተጨምሮበት እኚህን ወይዘሮ ዙፋንን ለአካልና ለሥነ-ልቦና ስቃይ ዳርጓቸው እንደነበረ ይገልጻሉ። ለበርካታ ዓመታት "ነገ የተሻለ ይሆናል" በሚል ተስፋ ረጅሙን ጊዜያት በስጋት አሳልፈዋል፡፡

የወይዘሮ አበባ ካሳ ሕይወትም የዚሁ ከባድ መከራ አካል ነበር። የዝናብ ውሃ ከጣሪያ ሲንጠባጠብ፣ የቆሻሻ ፈሳሽ ደግሞ በደጃፍ በኩል ሲፈስ፣ አሥር የቤተሰብ አባላት በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ተጨናንቀው ሌሊቱን የሚያድሩበት ሕይወት ለብዙዎች የቆየ መራራ እውነት ነበር። በዓል በመጣ ቁጥር ጎረቤት ተደስቶ ሲያከብር፣ ልጆቻቸውን በጠባቧ ክፍል ማሳደር አቅቷቸው ደጅ የሚያደሩበት ሁኔታ ከቤት ማጣት በላይ የእናትነት ልብን የሚሰብቅ ጥልቅ ቁስል ሆኖ ቆይቷል።

ይህ ሁኔታ መኖሪያ ቤት የጥላ ማረፊያ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ክብርና ደህንነት መሠረት መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በአሁኑ ወቅት የወይዘሮ አበባ ሕይወት ሙሉ በሙሉ አዲስ ምዕራፍ ይዟል። ከአንድ ጠባብና ከተበላሸች ክፍል ወጥተው ሙሉ ቁሳቁስ የተሟላለት የሁለት መኝታ ቤት ባለቤት መሆናቸው፣ በሥነ-ልቦናቸውና በጤናቸው ላይ ትልቅ እፎይታን ፈጥሯል።

እንደአልጋ፣ ሶፋና ፍራሽ ያሉ መሠረታዊ የቤት ቁሳቁሶች መሟላታቸውም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ ዜጎችን በቀጥታ ወደተሻለ የሕይወት ማዕረግ ያሸጋገረ ተግባር ነው። "አሁን መንፈሴ ተረጋጋ፤ የልቤ መሻት ሞላልኝ" የሚሉት የወይዘሮ አበባ ንግግር፣ የሰው ልጅ ክብሩና መብቱ ሲጠበቅለት የሚሰማውን የውስጥ ሰላም ያንጸባርቃል።

ወይዘሮ ዙፋን ስጦታውን እና ወይዘሮ አበባ ካሳን ተጠቃሚ ያደረገው ደሳሳ ቤቶችን አፍርሶ በተሻለ ህንፃ የመተካት መርሃ ግብር ነው፤ ከዚህ ቀደም ደሳሳ ቤቶችን ባሉበት መልሶ ማደስ ላይ ያተኩር የነበረው አሰራር ቀርቶ በቦታው የተሻለ ህንፃ ገንብቶ ብዙሃኑን ተጠቃሚ የማድረግ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ይህ ስራ ቀላል ግምት የማይሰጠው ጥቅም እያስገኘ ነው፤ በግል ደረጃ እንደተከናወነ የበጎ አድራጎት ተግባር ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይልቁንም ይህ እውነታ ከሕዝብ ተጠቃሚነት፣ ከማኅበራዊ ፍትሕ መንገስ እና ከዘመናዊ የከተማ ልማት አቅጣጫ አንጻር ጭምር እንጂ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ሂደቱ ሰብዓዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የከተማ እድሳት አቀራረብን ያንጸባርቃል። የከተማ የመልሶ ማልማት ሥራዎች የህንፃዎችንና የመሠረተ ልማትን ውበት ብቻ ትኩረት አድርገው ሊከናወኑ አይገባም። ይልቁንም የካፒታል አቅም የሌላቸውንና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም አረጋውያንንና አካል ጉዳተኞችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ሰብዓዊ ክብራቸውን መጠበቅ የልማቱ ቀጥተኛ ግብ ሊሆን እንደሚገባ ይህ አሰራር ያረጋግጣል።

በሁለተኛ ደረጃ፣ የሕዝቡ ማኅበራዊ ትስስር ሳይበታተን እንዲቀጥል የሚያስችል አሰራር መከተሉ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ነዋሪዎቹ

> **"ሰብዓዊ ክብርንና ማኅበራዊ ትስስርን ማዕከል ያደረገ የከተማ መልሶ ማልማት ተግባር፣ የከተሞችን መልክ ከመቀየር ባለፈ የማኅበረሰብ አብሮነትንና ዘላቂነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ እርምጃ ነው"**

ለረጅም ዓመታት ዕርስ በዕርስ በመደጋገፍ የገነቡትን ማኅበራዊ ትስስር ሳይበታተኑ በአንድነት አዲስ መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ መደረጉ፣ የማኅበረሰቡን አንድነት እና አብሮ የመኖር ባህል ሳይደፈርስ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ አርአያነት ያለው አሰራር መሆኑን ያሳያል።

በተጨማሪም፣ ፕሮጀክቱ የማኅበረሰቡን የተስፋና የሞራል ግንባታ የሚያጠናክር አዎንታዊ ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ አለው። ወይዘሮ ዙፋን ከተቀበሉት ቁሳዊ ጥቅም በላይ፣ የልማት ፍሬዎች ማኅበራዊ ፍትሕን ሲያረጋግጡ በዜጎች ዘንድ የሚፈጠረውን ቀና ስሜትና የነገ ተስፋ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የእነዚህ እናቶችን ሕይወት በዘላቂነት መለወጥ የመንግሥት የልማት ቃል-ኪዳን ከወረቀት ወደ ተግባር ሲቀየር በዜጎች ሕይወት ላይ የሚያመጣውን እውነተኛ ደስታ፣ ሥነ-ልቦናዊ እፎይታ እና የተስፋ አድማስ በግልጽ ያሳያል።

በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሄደ ባለው የከተማ መልሶ ማልማት ዙሪያ አስተያየታቸውን የሰጡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥናት መምህር እና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መሳይ ሙሉጌታ፣ ነዋሪዎች ሳይፈናቀሉ በነበሩበት አካባቢ በመልሶ ማልማት ተግባር ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ፕሮፌሰሩ የከተማ ቦታዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው በመሆናቸውና በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሰብዓዊ ደረጃ በታች በሆኑ ደካማ ቤቶች ውስጥ በጠበበ ሁኔታ በመኖራቸው፣ ቦታዎችን በአግባቡና በውጤታማነት ለመጠቀም የመልሶ ማልማት ስራዎች መካሄዳቸው አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ።

ለዚህ አይነቱ የመልሶ ማልማት ተግባር በደቡብ ቻይና የሚገኘውን የሸንዝሆን (Shenzhen) ከተማ በምሳሌነት ያነሱት ፕሮፌሰር መሳይ፣ ከ40 ዓመታት በፊት ከተማዋ አነስተኛና ከደረጃ በታች የሆኑ ቤቶች በሰፊ ቦታ ላይ የተበተኑባት፣ አብዛኛው ህዝቧም በዝቅተኛ ገቢ ላይ የተመሰረተ ኑሮ የሚመራበት የወደብ አካባቢ እንደነበረች ያስታውሳሉ። የቻይና መንግስት የመልሶ ማልማት አዲስ ፖሊሲ በመቅረጽ አካባቢዋን ወደ "ቻይና ኒው ዮርክ" ለመቀየር አቅዶ መንቀሳቀሱን ገልጸዋል።

በሸንዝሆን የተካሄደው የመልሶ ማልማት ሞዴል ዋነኛው ጠንካራ ጎን ሰፊ ቦታ ይዘው የነበሩ አነስተኛ ቤቶችን በመሰብሰብ ደረጃቸውን የጠበቁና ሙሉ ግልጋሎት ባሏቸው ህንፃዎች ውስጥ ነዋሪዎቹ አብረው እንዲኖሩ መደረጉ ነው።

ይህ የሸንዝሆን ተሞክሮ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማም እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን፣ ለምሳሌ በአቧሬ፣ ልደታ እና በቤተ መንግስት ጀርባ የተገነቡት ህንፃዎች አነስተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ሳይፈናቀሉ እዚያው እንዲኖሩ የተደረገበት አሰራር በጣም የሚደነቅና ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎች መሆኑን ፕሮፌሰር መሳይ ጠቁመዋል።

ነዋሪዎች ሳይፈናቀሉ እዚያው ለዓመታት በኖሩበት አካባቢ የመልሶ ማልማት ተጠቃሚ የሚያደርጉ አቀራረቦችን መከተል ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን፣ ህዝቡ በመንግስት ላይ እምነት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ከፍተኛ የፖለቲካና የማህበራዊ ትስስር ጥቅም እንዳለው አፅንኦት ሰጥተው አብራርተዋል።

ሰብዓዊ ክብርንና ማኅበራዊ ትስስርን ማዕከል ያደረገ የከተማ መልሶ ማልማት አሰራር፣ የከተሞችን መልክ ከመቀየር ባለፈ የማኅበረሰብ አብሮነትንና ዘላቂነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ እርምጃ ነው። ነዋሪዎችን ከለመዱት አካባቢና ከገነቡት ማኅበራዊ ትስስር ሳይበታተኑ በነበሩበት ስፍራ የመልሶ ማልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ፣ የቆየውን የጉርብትና እሴትና አብሮ የመኖር ባህል ሳይደፈርስ እንዲቀጥል ያስችላል።

ከኢኮኖሚ አንጻር ሲታይም፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የከተማ ቦታዎች ከአነስተኛና ከደረጃ በታች ከሆኑ ግንባታዎች ነፃ በማድረግ በውጤታማነት መጠቀም፣ ለአጠቃላይ የከተማዋ ዕድገትና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ትልቅ አቅም ይፈጥራል። በመሆኑም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከማኅበራዊ ፍትሕ ጋር የሚጣጣምበት የልማት አቅጣጫ፣ የከተሞችን ዘመናዊነትና ውበት ከማረጋገጡም በላይ ሁለንተናዊ እድገትን የሚያፋጥን አስተማማኝ መንገድ ነው።


SIKET BANK
መልካም
አዲስ ዓመት!
ደስታ እና ስኬት የበዛበት ዘመን
እንዲሆንልዎ እንመኛለን።
በመጪው ዓመት ለፋይናንስ ስኬትዎ አጋር
በመሆናችን ታላቅ ክብር ይሰማናል።
ሲኬት ባንክ
የስኬትዎ መሰረት!
www.siketbank.com
8342
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!
SWIFT
SSHCETAA


የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማት ከተማዋን ፅዱ፤ እንደ ስሟም ውብ እና አበባ በማድረግ ለማህበራዊ፣ ለመዝናኛ፣ ለስፖርትና ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አዳዲስ ዕድሎችን የፈጠረ የከተማ ልማት መድረክ ሲሆን፤ የሕፃናት መጫወቻዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የፓርኪንግ አገልግሎቶች፣ የእግር ኳስ፣ የመረብ ኳስና የባስኬት ሜዳዎች፣ የመሮጫና የሳይክል መንገዶች፣ የከተማ ግብርና፣ የመዝናኛና የቱሪዝም አገልግሎቶች ለነዋሪዎችና ለንግዱ ማህበረሰብ ተጨማሪ የተጠቃሚነት ዕድሎች ናቸው።
እንደ አራዳ ፓርክ፣ ስፖርት ፓርክ፣ የቀበና ሰው ሰራሽ ሐይቅና የጀልባ ሽርሽር፣ የወንዝ ዳርቻ የጎልፍ ካርት (Golf Cart) ሽርሽር፣ የድል ፕላዛ፣ የችሎትና የአፍሪካ ሕብረት ፓርኪንጎችን የመሳሰሉት ስፍራዎች ልማቱ ከመሠረተ ልማት ባሻገር ለአገልግሎትና ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የፈጠረውን ዕድል ያሳያሉ። በእንጦጦ–ቀበናና እንጦጦ–ፒኮክ የወንዝ ዳርቻ መስመሮችም አካባቢያዊ ንግድና መዝናኛ እንዲያድግ የሚያስችሉ አዳዲስ አቅሞች ተፈጥረዋል።
ተቋማት፣ ባለሀብቶች፣ ነጋዴዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎችና ግለሰቦች ከኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማቱ ጋር በመተባበር መስራት አዲስ የንግድ፣ የመዝናኛ፣ የቱሪዝም፣ የስፖርትና የአገልግሎት ዕድሎችን መፍጠርና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ችለዋል።
ከተማዋ መሠረተ ልማቱን ፈጥራለች፤ አሁን ዕድሉን ወደ እድገት መቀየር የሁላችንም ድርሻ ነው። መሰረተ ልማቶችን በጋራ እንጠብቅ፤ በጋራ እንጠቀም።
“ሰውን ማዕከል ያደረገ የአዲስ አበባ አዲስ ገፅታ፤ ከልማት ወደ ዕድል፤ ከዕድል ወደ ተጠቃሚነት!”
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን
2019

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም

ቴሌብር
telebirr

አዲስ

ጅማሮ!
ተስፋ!
እይታ!

፳፻፲፱ ዓ.ም
2019

በሰላም፣ በደስታ እና በፍቅር የተሞላ ብሩህ
አዲስ ዓመት እንዲሆንልዎ ከልብ
እንመኛለን!

መልካም
አዲስ ዓመት!



የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility



የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመላው ኢትዮጵያዊያን እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅርና የተስፋ እንዲሆንላችሁ ይመኛል! ተቋሙ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባለቤቶች አስተማማኝና ፈጣን የቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎችን ገንብቶ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው!

በመዲናችን አዲስ አበባ የገነባናቸው የቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎቻችን አድራሻ፡

- ሰዓሊተ ምህረት፡- ከማዕድን ሚኒስቴር ፊት ለፊት
- ፒያሳ፡- በኤሌክትሪክ ህንፃ (በቀድሞው ዋና መሥሪያ ቤት ግቢ)
- ቂሊንጦ ኮዬ ፈጬ አካባቢ በሚገኘው ቂሊንጦ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን (IPDC) ግቢ ውስጥ

የአገልግሎት የክፍያ፡-

- ከምሽቱ 4:00 እስከ ጠዋቱ 12:00 ሰዓት፡ 14.85 ብር /በኪሎ ዋት
- ከጠዋቱ 4:00 እስከ ቀኑ 11:00 ሰዓት፡ 16.57 ብር /በኪሎ ዋት
- ከቀኑ 11:00 እስከ ምሽቱ 4:00 እንዲሁም ከጠዋቱ 12:00 እስከ 4:00 ሰዓት፡ 18.28 ብር /በኪሎ ዋት

በዘመናዊው ቴክኖሎጂ ይዘምኑ፤ ጊዜና ወጪዎን ይቆጥቡ

**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**

መልካም አዲስ ዓመት!! 2019

# ከበዓላት ሰሞን መሻገር ያለበት እሴት

**• ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የሚደረገው ማዕድ ማጋራት ከመረዳዳት አንጻር ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳለው ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

የአዲስ ዓመት ብርሃን ሲፈነጥቅ በየቤቱ ደስታና ተስፋ አብሮ ይበራል። በአዲስ ዓመት መሬት አረንጓዴ ዕፅዋትና አደይ አበባ የሚያጌጥበት፣ ወንዞች የሚጠሩበት፣ ነፋሱ ሳይቀር አዲስ ተስፋን የሚያበስርበት፣ ሰዎች ተስፋን ሰንቀው በአዲስ ጉልበት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚነሳሱበት ወቅት ነው። ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላው ለመሸጋገር መነሳሳትን የሚፈጥር ልዩ የሕይወት ድልድይም ጭምር ነው፡፡

በዓሉ ይበልጥ የሚታወቀው ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ ወዳጅ ዘመድ በመሰባሰብ የሚያከብረው በመሆኑ ነው፡፡ በዕለቱ የኢትዮጵያውያን ቤቶች በደስታና በፈገግታ ይሞላሉ፤ የየቤቱ ማዕድ እንደየአቅሙ ይሰናዳል፤ የ"እንኳን አደረሳችሁ" መልካም ምኞት መላላክም የተለመደ ነው። አብሮ ማዕድ በመካፈል፣ በመጠጣት፣ እንዲሁም እርስ በእርስ በመጠያየቅ በድምቀት ይከበራል፡፡

አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ፣ ደስታና ማህበራዊ ትስስር ጎልቶ የሚታይበት ደማቅ በዓል ነው፡፡ ከዚህ የምስራችና የደስታ ድምቀት ባሻገር ግን በእነዚህ የበዓል ቀናት መጠጊያ ያጡ፣ የዕለት ጉርስ የሚያጥራቸው፣ አስታዋሽ ያጡ፣ የቅርብ ረዳት የሌላቸው በርካታ ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች በዓሉን በብቸኝነት፣ በችግርና በቁዘማ ቤታቸውን ዘግተው እና ተከፍተው እንዳያሳልፉ ካለው ማካፈልና መረዳዳት የቆየ የኢትዮጵያውያን የደግነት ባህላችን አለ፡፡

በአዲስ አበባ በተለምዶ ፈረንሳይ 41 ኢየሱስ በሚባለው አካባቢ የሚኖሩት ወይዘሮ ትዕግስት ይርጉ የሶስት ልጆች እናት ናቸው፡፡ የራሳቸው የሚሉት ቋሚ ስራ ስለሌላቸው ባለቤታቸው በቀን ስራ በሚያገኙት ገቢ ነው ኑሯቸውን የሚመሩት፡፡ በዚህ ምክንያት ህይወታቸው ከእጅ ወደ አፍ የሚባል ነው፡፡ እንደ አዲስ ዓመት ያሉ በዓላት ሲመጡ ካላቸው ለልጆቻቸው የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት በተቻለ መጠን ደስ ብሏቸው ለማሳለፍ ይሞክራሉ፡፡ ሳይኖራቸውና ሳይሞላላቸው ሲቀር ደግሞ በዓልን እንደማንኛውም ተራ ቀን ደስታ ርቋቸው ያሳልፉ ነበር፡፡

ከዚህ ባሻገር ግን በጎ አድራጊዎች በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ለቤት የሚያስፈልገው ሳይጎድልባቸው በዓልን በደስታ እንደሚያሳልፉ የሚናገሩት ወይዘሮ ትዕግስት፣ "ዓመት በዓል ሲደርስ 'እንዴት ነው የማሳልፈው?' እያልኩ እጨናነቃለሁ፤ በጎ አድራጊዎች የሚያደርጉት ድጋፍ ግን ቤተሰቦቼን 'ምን አበላቸዋለሁ? እንዴት አከብረዋለሁ' ብዬ ሳልጨነቅ ደስተኛ ሆኜ እንዳሳልፍ አድርጎኛል፡፡ ድጋፍ ላደረጉልኝ በጣም አመሰግናለሁ" ሲሉ የተሰማቸውን ስሜት በምስጋና ገልጸዋል፡፡

በበጎ አድራጊዎች ልብስና የልጆች ዳይፐር ጀምሮ ዱቄት፣ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ሽንኩርት፣ ዘይት እና መሰል የቤት ውስጥ ፍጆታዎችን ድጋፍ የሚያገኙት ወይዘሮ ትዕግስት፤ እንደዚህ አይነት ድጋፍ የሚያደርጉ ደጋግ ሰዎች ቁጥራቸው ሊበራከት እንደሚገባ ያምናሉ፡፡ ልጆቻቸውን ብቻቸውን ለማሳደግ አቅም የሚያንሳቸውን፣ የቅርብ አስታማሚና ረዳት የሌላቸውን እንዲሁም አቅመ ደካሞችን መደገፍና ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ህብረተሰቡና መንግስትም በየአካባቢው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች በመደገፍ በመተባበር በኩል እየሰራቸው ያሉ ስራዎችን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ያክላሉ፡፡



ፎቶ፡- ከፋይል

የነገን ናፋቂዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት አባላት ለተቸገሩ ወገኖች ለበዓል ድጋፍ ሲያደርጉ

ሌላኛዋ የአካባቢው ነዋሪ ወይዘሮ ሽብሬ ድሪባ ሶስት ልጆቻቸውን በብቸኝነት ያሳድጋሉ፡፡ የሚኖሩት በእናታቸው ቤት ሲሆን፣ ኑሯቸውን የሚገፉትም እናታቸው በጡረታ በሚያገኙት አነስተኛ ገቢ ነው። እንደ ወይዘሮዋ ገለጻ፣ ከዓመታት በፊት በመንገድ ስራ ላይ በቀን ሰራተኝነት ይሰሩ ነበር፡፡ ከበድ ያለ የጤና እክል ካጋጠማቸው ወዲህ እንደ ልብ ወጥተው መስራትና ልጆቻቸውን መመገብ ከባድ ሆኖባቸዋል። በዓል ሲመጣ በራሳቸው አሟልተው የሚያሳልፉበት ምንም አይነት አቅም የላቸውም፡፡

ሆኖም ጎረቤቶቻቸውና በጎ አድራጊዎች በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ኑሮን እየመሩ ይገኛሉ፡፡ በተለይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓል በመጣ ቁጥር ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ የነገን ናፋቂዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወጣቶች የበጎነት እጃቸውን በመዘርጋት ዱቄት፣ ዘይት፣ ስኳር፣ ዶሮና አልባሳትን ጨምሮ ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ሽብሬ በአስተያየታቸው፣ እንደ እኔ ላሉ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች የሚደረገው የደግነት እጅ ከበዓላት ባለፈ በሌሎች ቀናትም ቢቀጥል ጥሩ ነው፡፡ በችግር ውስጥ የምንኖር ሰዎች የምንበላውና የምንጠጣው ካገኘን ሌላውም ቀን ለኛ በዓል ነው፤ የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት እጃቸውን የሚዘረጉ ሰዎች ከበዓል ባለፈ በሌላውም ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ኪሎ በመስጠት ድጋፋቸውን ቢቀጥሉ ጥሩ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ከጎረቤት ጀምሮ በየሰፈሩ ያለው ማህበረሰብ የተቸገሩትን የመደገፍ ባህሉን ሊያጠናክር ይገባል" ብለዋል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ነዋሪ ወጣት ራውል ፔድሮ የበጎነት ተግባር አካል ነው፡፡ ወጣት ራውል እና ጓደኞቹ በ2012 ዓ.ም የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተከትሎ የእንቅስቃሴ ገደብ ሲጣል፣ በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉና አቅም የሚያንሳቸውን ሰዎች ለመርዳት 38 አባላትን ያቀፈ "ነገን ናፋቂዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት" መሰረቱ፡፡

በወቅቱ የምግብና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ከልዩ ልዩ በጎ ፈቃደኞች በማሰባሰብ ድጋፍ ማድረግ ጀመሩ። ከኮቪድ-19 በኋላም በአካባቢያቸው ወጥተው መስራት የማይችሉና አቅም የሌላቸው ወገኖች በመኖራቸው፣ ቢያንስ በየወሩ የሚያስፈልጋቸውን የቤት ፍጆታ ወጪ በመሸፈን ድጋፋቸውን ቀጠሉበት፡፡ ህብረተሰቡ በማህበሩ በኩል በሚያደርገው ድጋፍ፣ ማህበሩ ድጋፍ ከሚያደርግላቸው ሰዎች ባሻገር በበጎ አድራጎት ስራ ላይ ለተሰማሩ እንደ መቄዶኒያ፣ ጌርጌሴኖንና ሙዳይ ላሉ ድርጅቶችም ድጋፍ እንደሚያደርጉ የገለጸው ወጣት ራውል፣ ደም በመለገስ ጭምር የበጎ አድራጎት ማህበሩ በንቁ እየተሳተፈ እንደሚገኝ አክሏል፡፡

> **በየአካባቢው የሚኖሩና የተሻለ አቅም ያላቸው ዜጎች የጎረቤቶቻቸውን ህይወት፣ ውጣውረድና የዕለት ጉርስ ችግር በቅርበት ያውቃሉ። በመሆኑም የተቸገሩ ወገኖችን ልጆች በማስተማር፣ የአስቤዛና የኪራይ ወጪዎችን በመሸፈን ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው**

እንደ አዲስ ዓመት ያሉ በዓላት ሲመጡ ደግሞ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ለአንድ ቤተሰብ በአማካይ 20 ኪሎ ግራም የሚመዝን የቤት ውስጥ ፍጆታ ያቀርባሉ። ይህም 2 ሊትር ዘይት፣ 5 ኪሎ ሽንኩርት፣ 5 ኪሎ ዱቄት፣ ከ10 እስከ 15 እንቁላልና አንድ ዶሮ ያካተተ ነው፡፡ ከበዓላት ውጪ ባሉ ጊዜያት ደግሞ እንደ ሳሙና፣ ሶፍትና ዳይፐር ያሉ የንፅህና መጠበቂያዎችንና ደረቅ ምግቦችን ለተቸገሩ ወገኖች ያደርሳሉ።

ወጣት ራውል እንደሚናገረው ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች እርዳታ ሲያደርጉ ከተቀባዮቹ በላይ ደስ የሚለው እሱና የማህበሩ አባላት ናቸው፡፡ "እነዚህ ዜጎች ያለምንም መደበቅ ያለባቸውን ችግር ይነግሩናል፡፡ ተሯሩጠን ካላቸው ሰዎች በማሰባሰብ በዓልን እንደ ጎረቤቶቻቸው ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ እናደርጋለን፡፡ በሚደረግላቸው መጠነኛ ድጋፍ ፊታቸው ላይ የሚታየው ፈገግታና ደስታ በጣም ያረካል" ሲል ስሜቱን ይገልጻል፡፡

ለተቸገሩ ወገኖች የሚደረገው ድጋፍ ከበዓል ባለፈ ቀጣይነት ያለው መሆን እንዳለበት ወጣት ራውልም ይስማማል። የቤት ኪራይና የአስቤዛ ወጪ ከመሸፈን ባለፈ፣ ሰርተውና ቆጥበው ራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ መስሪያ ቦታ ወይም ጉሊት ላይ የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ባለሀብቶችና ህብረተሰቡ እጃቸውን ሊዘረጉ እንደሚገባ ያነሳል፡፡

በየአካባቢው የሚኖሩና የተሻለ አቅም ያላቸው ዜጎች የጎረቤቶቻቸውን ህይወት፣ ውጣውረድና የዕለት ጉርስ ችግር በቅርበት ያውቃሉ፡፡ በመሆኑም የተቸገሩ ወገኖችን ልጆች በማስተማር፣ የአስቤዛና የኪራይ ወጪዎችን በመሸፈን ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ይመክራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዘላቂነት ያለው ስራ ለመስራት መንግስት፣ ማህበረሰቡና ባለሀብቱ በቅንጅት መስራት አለባቸው ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

የ"ነገን ናፋቂዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት"ን በማሳያነት አነሳን እንጂ በመንግስትም ሆነ በግለሰቦች ደረጃ ድጋፍ የሚሹ ወገኖችን የማገዙ ተግባር እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ ይህ ባህል እንዲሆን፣ ከትውልድ ትውልድም እንዲሻገር ማድረግ ያስፈልጋል። የዘርፉ ምሁራን የሚያነሱት ሀሳብ ይኼንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

መስጠት እና በጎ ማድረግ ተፈጥሯዊና ባህላዊ መልክ ያለው መሆኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመራማሪ እና የሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህር ደሳለኝ አምሳሉ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን ያስረዳሉ። ከወዳጅ ዘመድና ጎረቤት ጋር አብሮ መብላትና ማሳለፍ እንዲሁም የተቸገሩትን መርዳትና መደገፍ የቆየ የኢትዮጵያውያን ድልብ ማህበረሰባዊ እሴት ነው። በተፈጥሮ ሰዎች የማዘን፣ የማካፈል እና የማጋራት ደመነፍሳዊ ፍላጎት አላቸው። በዚህ መሀል ግን ይህንን እንዳይወጡ የሚያደርጉ የአቅም እና የተለያዩ ውስንነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

ደሳለኝ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣ በበዓላት ወቅት በጎረቤት፣ በሰፈር እና በአካባቢ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች ምግብና መጠጥ ማካፈል፣ በዓልን አብሮ ማሳለፍ፣ እንዲሁም ጉብኝት በማድረግ 'አለሁላችሁ' ማለት ይገባል። የተቸገረን መርዳት እና መደገፍ ኃይማኖታዊ ግዴታ የመወጣት እንዲሁም የሰብአዊነት ጉዳይም ነው። "አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሲሰጥ ወይም ድጋፍ ሲያደርግ ለራሱም ደስታ ለማግኘት ጭምር ነው፤

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

# “እኔ ከጨለማ ወጥቻለሁ፤ ለሌሎችም የብርሃን መንገድ ማሳያ መሆን እፈልጋለሁ”

## የ‘ለነገዋ’ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚ ወጣት ሰብለ ለማ

**በለይላ መሐመድ**

ትውልድና እድገቷ በወሊሶ ከተማ የሆነው ወጣት ሰብለ ለማ (ስሟ ለዚህ ጽሑፍ ሲባል የተቀየረ)፣ ገና በለጋ እድሜዋ ነበር በከባድ ፈተና መፈተን የጀመረችው። የህይወት ጉዞዋ አልጋ በአልጋ አልነበረም። ገና በ16 ዓመቷ ተዳረች፤ ራሷ ከልጅነት ሳትወጣ ልጅ መውለድ ግድ ሆነባት። የእህል ውኃ ነገር ሆኖ ብዙም ሳትቆይ በቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምክንያት የፍቺ መራራ ጽዋን ለመጎንጨት ተገደደች። በልጅነት የተቀለሰው ጎጆ ፈረሰ፡፡ ሰብለ ህፃን ልጇን ለእናቷ በመስጠት “ከገጠር ከተማ ይሻላል” በሚል እምነትና የተሻለ ህይወትን ፍለጋ አቅጣጫዋን ወደ አዲስ አበባ አደረገች።

ይሁን እንጂ አዲስ አበባ ስትገባ ያሰበችውንና የተመኘችውን መልካም ህይወት ልታገኝ አልቻለችም። ይልቁንም ህይወት ወደ አልተመኘችው አሰቃቂ የጎዳና ህይወት ገፋቻት። መፅናኛና ደጋፊ ያጣችው ሰብለ፣ ህይወቷን ለማቆየት ስትል ሰውነቷን ለሽያጭ አቅርባ በሴተኛ አዳሪነትና በጎዳና ተዳዳሪነት ለመኖር ተገደደች። ጎዳና ላይ የገጠማት ህይወት ጨለማና መራራ ነበር፡፡ በሱስ መስከር፣ ረሃብ፣ ጥም፣ የሌሊት ውርጭና የሰዎች አረመኔያዊ ጥቃት የዕለት ተዕለት ገጠመኟ ሆኑ።

ለአራት የተደፈረችበትን መጥፎና ዘግናኝ አጋጣሚ ስታስታውስ የሚወርደውን የእንባ ዘለላዋን ለመሸሸግ አንገቷን በሐዘን ሰበር አድርጋ መሬት መሬቱን ታያለች። አቅም በማጣቷ ምክንያት በሸራ በተሰራች አነስተኛ ጎጆ ውስጥ ከመሰል ጓደኞቿ ጋር ውሎና አዳር ስታደርግ ቆየች። ወዳላሰበችውና ወዳልተመኘችው አስከፊው ህይወት እንዴት እንደገባች ስታስብ ወደዚያ ጥቁር ህይወት ውስጥ የጎተታትን አጋጣሚ ዛሬም ድረስ ትረግመዋለች።

### ሱሰኝነትና ተስፋ የመቁረጥ አፋፍ

የጎዳናው ህይወት ያስከተለባትን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ስቃይ ለመሸሸግ ስትል ሱስ ውስጥ ገባች። ቀስ በቀስም ያለ ጫት፣ ሀሽሽና አረቄ መቆም እንኳ የማትችልበት የሱስ እስረኛ ሆነች። ሱሰኝነቷ ሌላ ጣጣ አመጣባት፡፡ ሰክራ አስፋልት ላይ ወድቃ የፊት ጥርሷ ተሰበረ፤ ጫት፣ ሲጋራውና አረቄው ሲደጋገም ከባድ የጨጓራ ህመም አመጣባት፡፡ “ስሜም ጠፍቶ ስጋዬንም እየሸጥኩ ለሱስ ብቻ መኖሬ ይበቃኛል፤ ራሴን ካልቀየርኩ መኖሬ ትርጉም የለውም” በማለት በገመድ ራሷን እስከ ማነቅ ደርሳ እንደነበርና ሰዎች ተረባርበው እንዳስጣሏት ታስታውሳለች።



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ

በ‘ለነገዋ ’ የሴቶች ተሀድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል በዶሮ እርባታ ሙያ ሰልጥና የስራ እድል የተፈጠረላት ወጣት ሰብለ ለማ በስራ ላይ

### አዲሱ የህይወት ምዕራፍ

የሰብለን የጨለማ ህይወት የሚቀይር አጋጣሚ ተፈጠረ፡፡ አጋጣሚውም በአንድ ወቅት ጎዳና ላይ እያለች ተይዛ ወደ እስር ቤት ትገባለች። ከገባች በኋላ የሚጠይቃትም ሆነ የሚያስፈታት ዘመድ ባለመኖሩ እዛው እስር ቤት ውስጥ ለመቆየት ተገደደች፡፡ በዛ ተስፋ አስቆራጭ የእስር ቤት ህይወት ውስጥ እያለች የህይወቷን አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ የሚቀይር አጋጣሚ ተፈጠረላት። በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያው ቀውስ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን አሰልጥኖ የስራ እድል እየፈጠረ የሚገኘው የለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ የምትገባበት እድል አገኘች፡፡ ወደ ማዕከሉ ስትቀላቀል “ከእስር አመልጣለሁ” በሚል እንጂ ዘላቂ ተስፋ ይሆነኛል ብላ በመገመት አልነበረም። ይሁን እንጂ አጋጣሚው ያልጠበቀችውን አዲስ የህይወት ምዕራፍ ከፈተላት።

በማዕከሉ በነበራት ቆይታ በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መብላት ከማትችልበት ሁኔታ ወጥታ በቀን ሦስት ጊዜ የመመገብ እድል አገኘች። ማዕከሉ ባደረገላት የህይወት ክህሎት ስልጠና፣ ሁለገብ የአካልና የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የስፖርት እንቅስቃሴዎችና የህክምና ክትትል ከሱሷ ሙሉ በሙሉ እንድትላቀቅ አደረጋት፤ ሱስ ያቆሰለው ጨጓራዋም ዳነላት። የጤና ህክምናና የህይወት ክህሎት ስልጠናው ነገዋን በብሩህ ተስፋ እንድታይ አደረጋት። በመጨረሻም በዶሮ እርባታ ሙያ ሰልጥና በብቃት ለመመረቅ በቃች፤ ወዲያውኑም የስራ እድል ተፈጥሮላት ወደ ስራ ገባች።

### የአዲስ ዓመት ደስታና ዳግም ውልደት

“በአዲስ ዓመት አዲስ ህይወት፤ ለእኔ ደግሞ ዳግም ውልደት ነው” ስትል የቀኑን ግጥምጥሞሽ ታነሳለች። በጎዳና ህይወት ያለፈችባቸው መጥፎ ትዝታዎች የህይወቷ መጨረሻ ሳይሆኑ የለውጧ መነሻዎች ሆነዋል። ከማዕከሉ ከወጣች በኋላ ቤት ተከራይታ ኑሮዋን አሀዱ ማለት ጀመረች። በተሰጣት ስልጠናም በዶሮ እርባታ የስራ ዕድል ተፈጥሮላታል። ዛሬ ላይ ሰብለ ከማዕከሉ በተሰጣት መቋቋሚያ ብር የራሷን ቤት ተከራይታለች፡፡ ጤናዋም ተመልሶላታል፤ የተስፋ ብርሃን ፈንጥቆላትም አዲስ ህይወት መኖር ጀምራለች።

> “በአዲስ ዓመት አዲስ ህይወት፤ ለእኔ ደግሞ ዳግም ውልደት ነው”

ዘንድሮ የምታከብረው የ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት ለእሷ ተራ አዲስ ዓመት አይደለም። ከቆሻሻና አሰቃቂ ህይወት የወጣችባቸውን ዓመታት ሽኝታ ወደ አዲስ የህይወት ምዕራፍ የተሸጋገረችበት በመሆኑ ደስታዋ ድርብ ድርብርብ ነው። “ሊሆን ይችላል ብየ ያላሰብኩት እድልና አጋጣሚ ነው” ስትል በደስታና በተስፋ በተሞላ ድምፅ ትናገራለች። ከጎዳና ሸራ ወደ የራሷ ቤት፣ ከሱስ ወደ ጤና፣ ከተስፋ መቁረጥ ወደለመለመ ተስፋ የተሸጋገረው የወጣቷ የህይወት መስመር ማንኛውም በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚኖር ሰው ህይወቱ ሊቀየር እንደሚችል የሚያሳይ ህያው ምስክር ነው። የሰው ልጅ በምንም ዓይነት የጨለማ የህይወት መንገድ ውስጥ ቢገባ የመመለሻ በር እንዳለ ያሳያል። እሷም ያለፈውን ህይወቷን እንደ ትምህርት ትመለከታለች።

### የወደፊት ርዕይ

“እኔ ከጨለማ ወጥቻለሁ፤ ከዚህ በኋላ ለሌሎች የብርሃን መንገድ መሆን እፈልጋለሁ” በማለት የወደፊት ህልሟን ትገልጻለች፡፡ ራሷን ድጋሜ ወደ ሱስ ሊወስዳት የሚችለውን ማንኛውንም በሮችና መንገዶች ከመዝጋትና ከመፅናት ባለፈም በሱስ ውስጥ ተደብቀው የሚኖሩ እህቶች ከችግር እንዲወጡና ወደ ቀጥተኛው የመልካም ህይወት መንገድ እንዲሄዱ ማሳየት ትሻለች። ትናንት ከሱስና ከጎዳና ህይወት ጋር ስትታገል የነበረችው ሰብለ ዛሬ ለሌሎች መካሪ መሆን መቻሏ የሚበረታታ አርአያነት ያለው ተግባር ነው እያልን አዲሱ ዓመት መልካም የስራና የለውጥ ዘመን እንዲሆንላትም ምኞታችን ነው።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኘው ለነገዋ የሴቶች ተሀድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያው ቀውስ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን በማብቃት በከተማዋ እያንዳንዱ እንቅስቃሴና ልማት ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ በልዩ ትኩረት እየሰራ ይገኛል። እስካሁንም ለ5ኛ ጊዜ ስልጠና የሰጠ ሲሆን 3 ሺህ 259 ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል፡፡

# እቅዶቻችንን እንዴት እናሳካ?

**በጊዜው አማረ**

የአዲስ ዓመት መባቻ በሰዎች ስነ ልቦና እና በዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ በርካታ አወንታዊና በጎ ተጽዕኖዎችን ያሳድራል። ሰዎች ያለፈውን ዓመት ውጣ ውረድ በመተው፣ ለአዲሱ ዘመን አዲስ ተስፋ እና ብሩህ እይታን ይሰንቃሉ። ይህ አጋጣሚ በሰዎች አእምሮ ውስጥ አዲስ ተስፋን በመፍጠር ያለፉ ስህተቶችን ለማረም እና የነበሩ ተስፋ መቁረጦችን በማስወገድ አዲስ መንፈስ እና ተነሳሽነት ለመላበስ ትልቅ በር ይከፍታል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አዲስ ዓመት የሰዎችን አእምሯዊ ውጥረት በመቀነስ እፎይታንና ሰላምን ይሰጣል። በበዓሉ ሰሞን የሚኖሩ ማህበራዊ መሰባሰቦች፣ የምስጋና ባህሎች እና በጋራ የሚደረጉ በጎ ተግባራት በሰዎች አእምሮ ውስጥ አዎንታዊ ለውጦች እንዲሰፍኑ ያደርጋሉ። ይህም የጭንቀትና የድብርት ስሜቶችን በመቀነስ፣ አእምሮ ከአሮጌው ዓመት ድካም እና ጫና ተላቅቆ በበጎ አስተሳሰብ እና በተረጋጋ መንፈስ እንዲሞላ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ይላሉ፤ የስነ ልቦና ባለሙያዎች።

በተጨማሪም አዲስ ዓመት ግልጽ የሕይወት ግቦችን ለመቅረጽ እና እቅዶችን ለማቀድ አመቺ ወቅት ነው። ሰዎች በዚህ ወቅት ያለፈውን አፈጻጸማቸውን በመገምገም በሙያቸው፣ በትምህርታቸው፣ በጤናቸው እና በግል ሕይወታቸው ላይ አዳዲስ ግቦችን ያስቀምጣሉ። እንዲህ አይነት እቅድ ማውጣት ለሕይወት ግልጽ ዓላማ እና አቅጣጫ ስለሚሰጥ፣ ሰዎች ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ፣ አዳዲስ መልካም ልምዶችን እንዲያዳብሩ እንዲሁም ለበለጠ ስኬት እንዲተጉ ያነሳሳቸዋል ይላሉ፤ የስነልቦና ባለሙያው አቶ ሽታው ካሳ።

አቶ ሽታው "የስኬት ስነ ልቦና" በሚል በማህበራዊ ትስስር ገጽ በተለይም በቴሌግራም ሃሳቦችን ያጋራሉ፡፡ የግል ስብእና ስልጠናዎችንም ይሰጣሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ አዲስ ዓመት ማህበራዊ ትስስርን እና የሰዎች ግንኙነትን በማጠናከር በኩል የጎላ ሚና አለው። በበዓል ሰሞን ከቤተሰብ፣ ከወዳጅ ዘመድ እና ከጎረቤት ጋር የሚደረጉ መጠያየቆች ያለፈውን ድከምትና ቂም ለመርሳትና አዲስ መንገድ ለመጀመር አቅም ይሆናሉ። የተቀየሙ ሰዎችን ይቅር ማለት እና ግንኙነቶችን ማደስ በአእምሮ ውስጥ ያለውን መጥፎ ስሜትና ቂም ያስወግዳል። ለዚህ ደግሞ አዲስ አመት ልዩ እድል ይፈጥራል፤ ምክንያቱም በአዲስ አመት ቤተሰብና ጎረቤት በጋራ ይሰባሰባሉ፡፡ እርድ ይከናወናል፡፡ ቡና ይፈላል፡፡ ቤተሰብ ይጠያየቃል፡፡ ይህም ሰዎች የባለፈው አመት ድክመታቸውን እንዲነጋገሩና ለአዲሱ አመት በአዲስ እቅድ፣ ወኔና ተስፋ እንዲነሱ ያደርጋል፡፡



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻ ጂፒቲ
የአዲስ ዓመት ዕቅድ ለማሳካት ከቀላል ተግባር መጀመር ተገቢነት አለው

እዚህ ጋር ግን ሁልጊዜም አንድ ሃሳብ ይነሳል፡፡ ይህም በአዲስ አመት የምናቅዳቸው ከማሳካት አንጻር ቀላል የማይባል ክፍተት አለ የሚል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ የሚጋራው ወጣት ሳሙኤል ስዩም፣ እኔ ብዙ ጊዜ ለአዲስ አመት አቅጃለሁ፡፡ ግን ያሳካሁት የተወሰነውን ነው ይላል፡፡

ወጣት ሳሙኤል ስዩም፣ "እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችን አዲስ ዓመት ላይ በትልቅ ሞራል በርካታ እቅዶችን እናቅዳለን፡፡ መጨረሻ ላይ የምናሳካው ጥቂቱን ወይም ምንም ሊሆን ይችላል፡፡" ሲል ሃሳቡን አጋርቷል።

እቅዶቻችን ሳይሳኩ የሚቀሩበት ምክንያቶች መካከል አንዱ ካለን እውነተኛ አቅም፣ ጊዜና የኑሮ ሁኔታ ጋር ሳይመጣጠኑ ስለሚቀሩ ወይም በስሜት ተነሳስተን ሊደረሱ የማይችሉ ከበድ ያሉ ስለሚሆኑ ነው። ሁለተኛው ዋና ምክንያት ደግሞ ከእቅድ ባሻገር ወጥ የሆነ ልማድና መርሃ-ግብር አለመኖሩ ነው። አዲስ ዓመት ሲደርስ የሚፈጠረው የደስታና የመነቃቃት ስሜት ከጥቂት ሳምንታት በኋላ እየቀዘቀዘ ሲሄድ፣ አብሮት የሚጠፋው ተነሳሽነት እቅዶቹ እንዲዘነጉ ያደርጋቸዋል። የስነ ልቦና ባለሙያው ሽታው፣ "የተወሰኑትን እቅዶች እንኳን ማሳካት መቻሉ ትልቅ ነገር ነው፡፡

> "የአዲስ ዓመት እቅዳችንን ከሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ መከለስ፣ ትንንሽ እርምጃዎችን በቋሚነት መውሰድ፣ ባስመዘገብናቸው ጥቂት ስኬቶች ላይ ተመስርቶ ወደፊት ተስፋ ማድረግና ሊሳኩ የሚችሉ እቅዶችን ማቀድ ያስፈልጋል"

እቅዳችን የማይሳካው ግን ግቡን ወደ ዕለታዊ ትንንሽ ልማዶች ከመቀየር ይልቅ በአንድ ጊዜ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት በመሞከራችን ምክንያት ነው" ይላሉ።

በእርግጥ ያቀድነውን ሙሉ በሙሉ አለማሳካታችን ለአዲስ አመት እቅድ ማውጣትን ሙሉ በሙሉ ዋጋ ቢስ አያደርገውም። ወጣት ሳሙኤል፣ "እቅድ ማውጣት ህይወታችን ሙሉ በሙሉ አቅጣጫ ቢስ እንዳይሆንና የተወሰነ መሻሻል እንድናመጣ ይረዳናል። እኔ በ2018 ዓ.ም ለመማር አቅጄ ነበር። እየተማርኩ ነው፡፡ የግሌን ቢዝነስ መጀመር አስቤ ነበር፤ እሱ በተለያየ ምክንት አልተሳካልኝም፡፡ ስለዚህ አንዱ መሳካቱ በራሱ ጥሩ ነው" ይላል፡፡

የስነ ልቦና ባለሙያው አቶ ሽታው፣ ሙሉ በሙሉ አለማሳካትን እንደ ውድቀት ከመቁጠር ይልቅ፣ እቅዶቻችንን ከሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ መከለስ፣ ትንንሽ እርምጃዎችን በቋሚነት መውሰድና ሳሙኤል እንዳደረገው ባስመዘገብናቸው ጥቂት ስኬቶች ላይ ተመስርቶ ወደፊት ተስፋ ማድረግና ሊሳኩ የሚችሉ እቅዶችን ማቀድ እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ፡፡

የአዲስ ዓመት እቅዶቻችን ስኬታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ በመጀመሪያ ደረጃ ግቦቻችን እውነተኛና ሊደረሱ የሚችሉ መሆን አለባቸው። እቅድ ሲታቀድ በስሜት ተነሳስቶ ከሚችሉት በላይ የሆኑትን ከመደርደር ይልቅ፣ አእምሮ በቀላሉ ሊቀበለውና ሊተገብረው የሚችለውን ግልጽና አነስተኛ ቁጥር ያለው እቅድ ማውጣት ያስፈልጋል። እቅዶቹ ሊለኩ የሚችሉና ከራሳችን ዕለታዊ ህይወትና አቅም ጋር የተጣጣሙ መሆን እንዳለባቸው ባለሙያው ያሳስባሉ።

እቅዶችን ለማሳካት ዋናው ቁልፍ ነገሮችን ወደ ዕለታዊና ሳምንታዊ ተግባራ መለወጥ ነው። አቶ ሽታው እንደሚገልጹት፣ ትልቅ አላማን በአንድ ጊዜ ለማሳካት መሞከር ለአእምሮ ድካም ስለሚፈጥር፣ እቅዱን ከፋፍሎ በየቀኑ በጥቂቱ መተግበር ይገባል። በተጨማሪም በተነሳሽነት ስሜት ላይ ብቻ ከመደገፍ ይልቅ ቋሚ ባህል ማድረግና መርሃ-ግብር ማበጀት፣ እንዲሁም የደረስንበትን ደረጃ በየጊዜው እየገመገሙ መሄድ እቅድን ወደ ስኬት ለመቀየር ወሳኝ መንገድ ነው።

እቅዶቻችን ባሰብነው መንገድ ሳይሳኩ ቢቀሩ ደግሞ፣ ራስን በወቀሳና በብስጭት መቅጣት ፍጹም ተገቢ እንዳልሆነ የስነ ልቦና ባለሙያው ይመክራሉ። አለመሳካት የውድቀት ማብቂያ ሳይሆን የአሰራር መንገዳችንን እንድንፈትሽ የተሰጠ ትምህርት ነው። ስለዚህ እቅድ ሳይሳካ ሲቀር ተስፋ ቆርጦ ሙሉ በሙሉ ከመተው ይልቅ፣ የተቀመጠው ግብ ከባድነቱን ወይም የራሳችንን ዝግጅት

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!
እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በንግድ ፣ በሆስፒታሊቲ እንዲሁም በኮንስትራክሽንና ሪል እስቴት ዘርፎች የተደራጁ 45 ኩባንያዎችን ያቀፈና ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ ተቋም ነው፡፡ ማህበራዊ ኃላፊነቱንም ለመወጣት ከትርፉ 10 በመቶውን በመመደብ እየሰራ ይገኛል፡፡
በተለያዩ አከባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ መንገድ፣ ንጹህ ውሃ፣ የወንዝ ዳር ልማት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታና ሌሎች ስራዎችን እየሰራ ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡
ወደፊትም ለሀገራችን የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ-የሀገር ሀብት



መልካም
አዲስ ዓመት!!
፳፻፲፱ | 2019

አቢሲንያ ባንክ
Bank of Abyssinia

እንኳን ለ2019 ዓ.ም. አደረሳችሁ!
አዲሱ ዓመት የሰላም ፣ የዕድገት ፣ የጤና እና የፍቅር እንዲሆንልዎ እንመኛለን!

መልካም
Happy New Year!
አዲስ ዓመት

፳፻፲፱ | 2026 2027




ተደራሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ.የተ.የሀ.ሥ.ማህበር
Tederash Saving & Credit Cooperative Society Ltd.

# እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!

ተደራሽ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ በዓሉ የሰላም የጤናና የፍቅር እንዲሆንላችሁ ይመኛል፡፡

የምንሰጣቸውአገልግሎቶች

1 የቁጠባአገልግሎት
- መደበኛ ቁጠባ
- የፍቃደኝነት ቁጠባ
- የጊዜ ገደብ ቁጠባ
- የንግድ/የቀን ገቢ ቁጠባ
- የቤት ቁጠባ
- የመኪና ቁጠባ
- የሴቶች ልዩ ቁጠባ
- የወጣቶች/ተማሪዎች ቁጠባ
- የህጻናት/ልጆች ቁጠባ
- የድርጅት ቁጠባ
- የኤሌክትሪክ መኪና ባትሪ ቁጠባ

2. ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት/ Interest Free Service

3. የብድር አገልግሎት
- በአዲስ ንግድ ስራ ለሚሰማሩ እና ለነባር ንግድ ማስፋፊያ
- ለቤት ግንባታ፣ ግዥና እድሳት
- ለኮንዶሚኒየም ክፍያ
- ለመኪና ግዥ
- ለኢንቨስትመንት
- ለስራ ፈጠራ
- ለማህበራዊ ጉዳይ፡ ለሕክምና፣ ለትምህርት ስልጠና ለንብረት ግዥና ዕድሳት፣ ለቀለበትና ጋብቻ
- ለብድር መድህን ዋስትና እንዲሁም የተለያዩ ኑሮን ለማሻሻል ለሚያስችሉ ጉዳዮች መበደር ይችላሉ፡፡

**ስልክ7078/0970444411/88/00**
**አድራሻ ዋና ቢሮ አራት ኪሎ ኢትዮጵያ ፖስታ ቤት**
**ትንሽ ቆጥበው ትልቅ ይሁኑ!**
**ተደራሽ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር**



ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ.የተ.የግ.ማ
Commercial Nominees P.L.C

**እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!**
**በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የደስታ ይሁንላችሁ!**

# መልካም አዲስ ዓመት!!
፳፻፲፱ | 2019

## የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

- የሰው ኃይል አቅርቦትና አስተዳደር
- የተሟላ የፅዳት አገልግሎት
- ሲ.ቢ.ኢ ብር ኤጀንት ባንኪንግ
- ንብረትና ሕንፃ ማስተዳደር
- ሕንፃዎችን መግዛትና መሸጥ
- የፈንድ አስተዳደር እና ገቢ መሰብሰብ
- ትዕይንት ማዘጋጀት
- ድርጅቶችን ማስተዳደር
- ጨረታ ማካሄድ (ማስተዳደር)
- የካሳና ሌሎች ክፍያዎችን መፈፀም
- የስልጠና ማዕከል ኪራይ አገልግሎት

**Address**
Head office
Seid Yasin Building (Bole behind Dembel City Center)
Phone:- +251 11 156 4350
Toll-Free:- 6630
P.O.Box:- 12413
Email:- info@commercialnominees.com
Website:- www.commercialnominees.com

# ልጆች አዲስ ዓመትን የምታከብሩት እንዴት ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
አበባ አየሽ ወይ ጭፈራ ልጆች በእንቁጣጣሽ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ተጠቃሽ ነው

ልጆች እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ፡፡ አዲሱን ዓመት በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላም እንደምትቀበሉት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ሀሳባችሁን ለቤተሰቦቻችሁ አካፍሎአቸው፡፡ ጓደኞቻችሁ በዓሉን እንዴት እንደሚያከብሩት እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ፡፡

አሜን የኔነህ እባላለሁ፡፡ 11 ዓመቴ ነው። እንቁጣጣሽን በተስፋና በጉጉት ነው የምጠብቃት፡፡ የበዓሉ ዕለትም ባህላዊ አልባሳትን በመልበስ፣ ከበሮና አደይ አበባ በመያዝ ከጓደኞቼ ጋር

“ሆ ብለን መጣን ሆ ብለን፤
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን፤
አባባ አሉ ብለን፤ እሜቴ አሉ ብለን...”

እያልን እንጨፍራለን፡፡

ትንሽ እንደጨፈርንም ዳቦም ሆነ ብር ይሰጠናል፡፡ እኛም “ከብረው ይቆዩን ከብረው፣ በዓመት ወንድ ልጅ ወልደው፤ ሰላሳ ጥጆች አስረው” እያልን አመስግነን እንወጣለን፡፡ ያገኘነውን ብርም ተከፋፍለን ከበዓሉ በኋላ ኬክ ገዝቼ እበላበታለሁ፡፡

ዳግም ዮሴፍ እባላለሁ፡፡ 15 ዓመቴ ነው፡፡ እንቁጣጣሽ የምንደሰትበትና አዲስ ዓመት የሚጀመርበት ነው፡፡ መሬቱ አበባ ለብሶ ለምልም ሳሩ ደምቆ የሚታይበትም ነው፡፡ ለዚህም እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ ለማለት የተለያዩ አበባዎችን እየሳልኩ ለቤተሰብና ለጎረቤት በመስጠት መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

ከጓደኞቼ ጋር የስዕል ስጦታ በማበረክትበት ብር ይሰጡናል፡፡ የአዲስ ዓመት የማይረሳ አንድ ገጠመኝ አለኝ። ከጓደኞቼ ጋር ሰብሰብ ብለን አንድ ቤት አንኳኩተን ስንገባ ውሻቸው ተፈትቶ ኖሮ አሯሯጠን፡፡ ከዚያም የቤቱ ባለቤት ይቅርታ ጠይቀውንና ውሻውን አስረውት የስዕል ስጦታችንን ሰጥተን እንደተመለስን አስታውሳለሁ፡፡

እንኳን አደረሳችሁ በምንልበት ወቅት የሚሰጠንን ብር ለቤተሰቦቼ እሰጣቸዋለሁ። እነሱም ከእነሱ ብር ጨምረው የሚያስፈልገኝን ነገር ይገዙልኛል፡፡

ነጠል ፀጋው እባላለሁ፡፡ 15 ዓመቴ ነው፡፡ አዲስ ዓመትን ለማክበር ከጓደኞቼ ጋር ጳጉሜን ጀምረን ለበዓሉ የሚሆን ባህላዊ ልብስ እናስገዛለን፤ ያልቻሉ ደግሞ ታጥቦ እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ፡፡ ከበሮ እና ብልጭልጭ ነገሮችንም እንቀራርጣለን፡፡ በዕለቱም በሃበሻ ቀሚስ አምረንና ተውበን “አበባ አየሽ ወይ......”፣ “ይሽታል ዶሮ ዶሮ የእማምዬ ጓሮ” በማለት ከጓደኞቼ ጋር በሰፈር ውስጥ እንጫወታለን፡፡ ስጦታዎችን እንደሰጡንም የመልካም ምኞት ስጦታ፤ “ከብረው ይቆዩን ከብረው....” እያልን እናመሰግናቸዋለን፡፡ ይህንንም የምንለው ደስታችንን ለመግለፅ ነው። የተሰጠንን ብር በመካፈል የምንፈልገውን ነገር እናደርግበታለን፡፡

በዓብ ገብረመስቀል እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው፡፡ አዲስ ዓመት ሲመጣ ቤተሰቦቼንና ጎረቤቶቼን እንኳን አደረሳችሁ ለማለት ለአዲስ ዓመት ሁለት ሳምንት ሲቀረው ስዕል በመሳል ስዘጋጅ እቆያለሁ፡፡ የምስላቸው ስዕሎችም የተለያዩ አበባዎችን ነው። እስከ 35 የሚደርሱ ስዕሎችን በመሳል አዘጋጃለሁ። የበዓሉ ዕለትም የሳልኳቸውን ስዕሎች በመያዝ እንኳን አደረሳችሁ እያልኩ በየቤቱ እሰጣለሁ፡፡ ስዕሎቹን ሰጥቼ እንኳን አደረሳችሁ ስላቸው ሁሉም ባይባልም አብዛኞቹ ብር ይሰጡኛል። እሱን ተቀብዬ በደስታ ወደ ቤቴ እመለሳለሁ፡፡

## አደይ አበባ



አደይ አበባ በሳይንሳዊ ስሙ Bidens macroptera በመባል ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚበቅል የዕፅዋት ዝርያ እና የሁዳዴ (Asteraceae) የእፅዋት ወገን አባል ነው። ይህ አበባ በኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

በተለይም የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት (እንቁጣጣሽ) በሚከበርበት በወርሃ መስከረም መጀመሪያ ላይ መስኮችን በብጫ ቀለሙ ያሸበርቃል፡፡ በዚህ አማካኝነትም የአዲስ ዘመን፣ የተስፋ እና የክረምት ማብቂያ (የጸደይ መባቻ) ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል።

አደይ አበባ ቀለሙ ደማቅ ብጫ ሲሆን ተምሳሌትነቱ አዲስ ተስፋ፣ ብርሃን እና የተፈጥሮ መታደስን ነው። የሚያብበውም ከነሐሴ መጨረሻ እስከ መስከረም(በተለይ በአዲስ ዓመት ማግስት) ጀምሮ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ስሙ የገነነው አደይ አበባ የዕይታ ጊዜው እንደስሙ ግዝፈት አይደለም፡፡ ተስፋ እና ደስታን ያንጸባርቃል የሚባለው ቢጫማ ቀለም ሀገር ምድሩን አልብሶ የሚቆየው ቢበዛ ለሶስት ወር እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህም የአደይ አበባ ሌላው መለያ ባህርይ ነው፡፡

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



# እንቆቅልሽ

## ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ላይጠቅማት ሸክሙ ባሳት?**

**መልስ፡- ሀ. የፍየል ጅራት**

## የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ላዩ ሰርዶ ውስጡ ብርንዶ?**

ሀ. ካሮት
ለ. ቀይ ሽንኩርት
ሐ. ድንች

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ራስን ከማብቃት የተሻገረው የዲጂታል ክህሎት

• የኮደርስ ሥልጠና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑ የትም ሀገር ሄዶ ለመሥራት እንደሚያስችል ተጠቁሟል

**በደረጀ ታደሰ**

በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም. በይፋ የተጀመረው የአምስት ሚሊየን ኢትዮ-ኮደርስ (5 Million Ethiopian Coders) ስልጠና ውጤቱ መታየት ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ በተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ እና በኢትዮጵያ መንግስታት የጋራ ትብብር በመተግበር ላይ ያለው መርሃ ግብሩ አራት መሰረታዊ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችን ማቅረቡ ይታወቃል፡፡ እነዚህ የሥልጠና ዘርፎች ዌብ ፕሮግራሚንግ (Programming Fundamentals)፣ በአንድሮይድ ማበልፀግ (Android Kotlin Developer)፣ ዳታ ሳይንስ (Data Science Fundamental) እና ሰው ሰራሽ አስተውሎት(Artificial Intelligence) ናቸው፡፡

በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በዕውቀትና ክህሎት የበቃ፣ በአገሩ ዲጂታል ኢኮኖሚ ላይ በንቃት የሚሳተፍ፣ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሚሆን የሠው ኃይል ለማፍራት መልካም አጋጣሚን ይዞ ከመጣው ከዚህ የሥልጠና ዕድል ብዙዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከቀረበው የ5 ሚሊዮን ሠልጣኞች ዕድል ውስጥ፤ አዲስ አበባም የራሷን ድርሻ ወስዳ እየተጠቀመች ትገኛለች፡፡ መርሃ ግብሩ ይፋ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የመዲናዋ ወጣቶች ሥልጠናውን ወስደው ማጠናቀቃቸውን የከተማ አስተዳደሩ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ መረጃ ያመለክታል፡፡

ሥልጠናው፣ መሰረታዊ ዕውቀትና ክህሎት ከማስጨበጥ አልፎ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ዕውን ለማድረግ አቅም እንደፈጠረ በርካታ ወጣቶች ምስክር ናቸው፡፡ እኛም በዚህ ጽሁፍ በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ያለውን አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን ብሎም ለማሻሻል ያስቻለ ውጤት ያመጡ ወጣቶችን ተሞክሮ እናቀርባለን፡፡

ወጣት አባይ አደሬ ይባላል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ ባለሙያ ነው፡፡ አራቱንም የኦንላይን የሥልጠና ዘርፎች ተከታትሎ በማጠናቀቅ ሰርተፊኬቱን ወስዷል፡፡ በምህንድስና ሙያ ዘርፍ የተመረቀው ይህ ወጣት፤ ከሥልጠናዎቹ ያገኘው ዕውቀት እና ክህሎት በውስጡ ያለውን እምቅ አቅም ወደ ጥቅም እንዲቀይር እንዳገዘው ይናገራል፡፡

"ኢትዮ ኮደርስ ሥልጠና መውሰድ የጀመርኩት፤ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አማካኝነት ይፋ እንደተደረገ ነው፡፡" የሚለው ወጣት አባይ፤ በሥልጠናው የተካተቱት ኮርሶች



ፎቶ፡- ከፋይል
ወጣት አባይ አደሬ የኢትዮ ኮደርስ ስልጠናዎችን በመውሰድ የተለየዩ ሶፍትዌሮችን የሠራ



ፎቶ፡- ከፋይል
ወጣት ምህረት ፍቃዱ የኢትዮ ኮደርስ ስልጠናዎችን ከመውሰድ ባለፈ በርካቶች ስልጠናውን እንዲወስዱ ያገዘች

በጣም መሰረታዊና ጠቃሚ መሆናቸውን በሂደቱም እንዲሁም ባገኘው ውጤትም ማረጋገጥ መቻሉን ይናገራል፡፡ "ሥልጠናዎቹን በግል ከፍሎ ለመውሰድ ይከብዳል፡፡ በኦንላይን ከሚሰጡ ሥልጠናዎች በአቀራረብ፣ በጊዜ እና በዘርፍ የተከፋፈሉ፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ መስክ ራስን ለማብቃት የሚያስችሉና መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እንዲህ አይነት ሥልጠና መንግስት በነጻ በማቅረቡ ሊመሰገን ይገባዋል" ብሏል፡፡

ከኢትዮ ኮደርስ ሥልጠና ራሱን በአዲስ ዕውቀትና ክህሎት የገነባው ወጣት አባይ፤ የጋን ውስጥ መብራት ሆኖ አልቀረም። ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ለሚሠራበት ተቋም (ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ) አገልግሎት የሚሰጡ ሶፍትዌሮችን አልምቶ ለአገልግሎት አብቅቷል፡፡ እንደ እርሱ ገለጻ ከሆነ፤ ከዚህ በፊት የሥራ ዕድል ፈጠራ መረጃ ይያዝ እና ይደራጅ የነበረበትን የማንዋል አሠራር ያስቀረ፤ ከምዝገባ ጀምሮ ያለውን ሂደት በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት ያዘመነና ያቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት Job Management System (JMS) አንዱ ነው፡፡ ከወረዳ እስከ ከተማ ድረስ ጥቅም ላይ የዋለው ሶፍትዌሩ፤ መረጃዎች ጥራት ባለው ሁኔታ እንዲደራጁ፣ ከሰው ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ፣ ለአንድ ሰው አንድ ሥራ ዕድል እንዲፈጠር እንዲሁም ግልጽና ፍትሃዊ አሠራር እንዲሰፍን፣ አግዟል፡፡

ሌላኛው የለማው ሶፍትዌር፣ የተገልጋይን እርካታ የሚያሻሽል (Smart Customer Service System) ነው፡፡ በተቋሙ ባሉ ሠራተኞች እና ተገልጋዮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያቀላጥፍ ሲሆን፤ ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያላቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየት በኦንላይን የሚሰጡበትን አሠራር መዘርጋት ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በግል ወይም በማህበር የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ሥራ ፈጣሪዎች፣ በኦንላይን አማካኝነት ምርቶቻቸውን ለተጠቃሚው የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበትን አሠራር ለመፍጠር ጥረት የተደረገበት (Corporate & E-Commerce Web Platform) በእሱና በጓደኞቹ አማካኝት ማልማት መቻሉንም አክሏል፡፡

ወጣት ምህረት ፍቃዱ፤ እንደ ወጣት አባይ በኢትዮ ኮደርስ የተፈጠረው የሥልጠና ዕድል በአግባቡ ተጠቅማለች። ዘመኑን የዋጀ ዕውቀትና ክህሎት በማግኘቷ፣ ራሷን አብቅታ ለሌሎች መትረፍ ችላለች፡፡ በከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አማካኝነት በኢትዮ ኮደርስ ሥልጠና አማካኝነት የተሻለ ውጤት ማምጣት ከቻሉ ትጉህና ብልህ ወጣቶች ከተካተቱበት የስኬት መዝገብ ላይ ስሟን ማስፈር ችላለች፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የምትኖረው እና በመንግሥት ተቋም ውስጥ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ባለሙያነት የምታገለግለው ወጣት ምህረት፤ ስለ ስልጠና መርሃ ግብሩ መረጃ የሰማችው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት ይፋ በተደረገበት ቅጽበት መሆኑን በማስታወስ፤ "መረጃውን እንደሰማሁ ጊዜ ሳልወስድ በዕድሉ ለመጠቀም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገባሁ፡፡ የሚሰጡት ሥልጠናዎች በጣም ጠቃሚ ስለነበሩ፤ የሥራ ጊዜዬን በማይነካ መልኩ አራቱንም ስልጠናዎች ተከታትዬ በብቃት በማጠናቀቅ ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀት (ሰርተፊኬት) ማግኘት ችያለሁ።" በማለት አስረድታለች፡፡

ወጣት ምህረት፣ ከሥልጠናዎቹ ያገኘችውን ጠቀሜታም እንዲህ ታብራራለች፡፡ "አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎት ሰጥተውኛል፡፡ በሥራዬ ውጤታማ እንድሆን አግዞኛል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ በየጊዜው እየለሙ ለአገልግሎት የሚበቁ ሴፍትዌሮች እና ፕሮግራሞችን በአግባቡ ለመጠቀም፤ ለሌሎችም እገዛ ለማድረግ አስችሎኛል። የሰው ሠራሽ አስተውሎትን (Artificial Intelligence- AI) በመጠቀም ለሥራ አጋዥ የሆኑ የአኒሜሽን ፕሮግራሞችን በራሴ አቅም በማልማት ላይ እገኛለሁ፡፡"

"ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀው ይህ ሥልጠና የሚሰጠው በነጻ ነው፡፡ የኦንላይን ስልጠናዎች በነጻ አይገኙም። ይህ ስልጠና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑ፤ የትም ሀገር ሄዶ በሙያው መሥራት ያስችላል፡፡ አቅም የበለጠ ለማሳደግ መሰረት ይጥላል" የምትለው ወጣት ምህረት፤ ከእሷ ባለፈ በምትሠራበት ወረዳ ባሉ የመንግሥት ተቋማት የሚያገለግሉ ከ200 በላይ ሠራተኞች እንዲሰለጥኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩሏን ጥረት አድርጋለች፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሙያ አሰልጣኝ መሠረት ተሾመ፤ በሙያው ያላት ዕውቀትና ክህሎት አልገደባትም፡፡ ይልቁንም የኢትዮ ኮደርስ የነጻ ሥልጠና መርሃ ግብሮችን በአግባቡ በመከታተል አጠናቅቃለች። ከሥልጠናዎቹ አዳዲስ ዕውቀት እና ክህሎት እንዳዳበረች፣ ለሠልጣኞቿ የተሻለ የንድፈ ሃሳብም ሆነ የተግባር ሥልጠና ለመስጠት አቅም እንደፈጠረላት እንዲሁም በኮሌጃቸው ለአገልግሎት የሚበቃ ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጂ ለመሥራት እንዳነሳሳት ገልጻለች፡፡

"ዕድሉ በቀላሉ የማይገኝ ነው። ይህንን እንደ እኔ ዓይነቱ በሙያው ውስጥ ያለ ሰው በይበልጥ ይረዳዋል። በመርሃ ግብሩ የቀረቡትን አራት ኮርሶች ወስጄ፤ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሰርተፊኬት ተቀብያለሁ" የምትለው አሠልጣኝ መሠረት፤ በመደበኛ የማሰልጠን ተግባሯ ላይ ያስገኘላትን ውጤት እንደሚከተለው አስረድታለች፤ "የማሰለጥናቸው 25 ወጣቶች እነዚህን ኮርሶች እንዲወስዱ ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ እገዛ አድርጌያለሁ፡፡ ሰልጣኞቹም ከዕድሉ በሚገባ ተጠቅመዋል፡፡ ስልጠናውም ሙያቸውን በተግባር የሚገልጡበትን አቅም ፈጥሮላቸዋል። በሥልጠና ላይ እያሉ ያላቸውን ውስጣዊ አቅም እና ፍላጎት የበለጠ እንዲያውቁት አዲስ ነገር ሆኖላቸዋል። ኮዲንግ በመጠቀም የራሳቸውን የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እንዲሠሩ፣ ገጸ ድር እንዲያለሙ አግዟቸዋል፡፡ የመመረቂያ ፕሮጀክቶቻቸውን በጥራት እና በውጤታማነት እንዲሠሩም አቅም ሆኗቸዋል፡፡"

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ በ5 ሚሊዮን ኢትዮ ኮደርስ ፕሮጀክት ትግበራ ላይ በከተማ ደረጃ የአስተባባሪና መሪ ሚና እንደሚወጣ የጠቆሙት የቢሮው ኃለፊ አቶ አዋሌ መሐመድ፤ በየክፍለ ከተማው የኮምፒዩተርና የኢንተርኔት ማዕከላትን ማመቻቸት፣ የስልጠና አስተባባሪዎችን (Mentors) ማደራጀት፣ ሰፊ የምዝገባና የግንዛቤ ንቅናቄ የመምራት ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በስማርት ቴክኖሎጂ የተገናኘች (Smart Connected City) ማድረግ፣ የቴክኖሎጂ ፓርኮችን ማጠናከር፣ ወጣቶች በዲጂታል ስራዎች (Digital Freelancing) የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙበትን ማዕቀፍ ማስፋፋት እና ተያያዥ ተግባራት በቀጣይም ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸውን ያነሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ይህንን ውጤታማ ለማድረግ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት የበቃ የሠው ኃይል ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በ5 ሚሊዮን ኢትዮ ኮደርስ መርሃ ግብር የቀረቡ የሥልጠና ዘርፎችን መከታተል፣ ሠርተፊኬቱን መያዝ፣ ዕውቀትና ክህሎትን ወደ ተግባራዊ ውጤት መቀየር፣ በዓለም አቀፉ መድረክ ላይ ተወዳዳሪ መሆን እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡


ላይፍ ኃ/የተ/መ/ ቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበር
LIFE SAVING AND CREDIT COOPERATIVE Ltd.
አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዓመት ሲተካ አደይ አበባ ሲፈነዳ ዘመድ ከዘመዱ እንኳን አደረሳችሁ እየተባባለ ልዩ የአዲስ ዓመት ስጦታ ሲያበረክት፤ ላይፍ ቁጠባና ብድርም በየዓመቱ አዳዲስ የቁጠባና ብድር አማራጮችን ለማህበረሰቡ እያበረከተ ይገኛል፡፡
ያኔ በመቶ ሺዎች ካፒታል ስራውን ሀ ብሎ የጀመረው ላይፍ ቁጠባና ብድር አባላቱን ቤትና መኪና እያምበሸበሸ ከስኬት ማማ ላይ አድርሶ ዛሬ ላይ አንድ ቢሊየን ተቀማጭ ካፒታል ላይ ደርሷል፡፡
እርሶም በአዲሱ ዓመት ስኬታማ ዘመን እንዲያሳልፉ የሁል ጊዜ ምርጫዎ ላይፍ ቁጠባና ብድር ይሁን ይሎታል፡፡
ለቤት፣ ለመኪና፣ ለንግድ ማስጀመሪያና ማስፋፊያ በአጭር ጊዜና ቀልጣፋ አሰራር በከፍተኛ የብድር ጣሪያ እስከ 20 ሚሊየን ብር እኛ ጋር ያገኛሉ፡፡
በአዲሱ ዓመት ከልብ ለሚወዱት የሚበረከቱት ልዩ ስጦታዎችን እንንገሮት፤ የቤት ቁጠባ፣ የመኪና ቁጠባ፣ የንግድ ማስጀመሪያ አልያም ማስፋፊያ እና የህፃናት ቁጠባን በስጦታ ያበርክቱ፡፡
በአዲሱ ዓመት ከኛ ጋር አዲስ ቤተሰብ ለመሆን የቱ ቅርንጫፍ ይቀርቦታል? ዋናው ቢሮ 6 ኪሎ ቅርንጫፎቻችን አራዳ ጊዮርጊስ፣ ደጃች ውቤ፣ ሀያ ሁለት፣ ጀሞ 1፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ በክልል ከተሞችም አዳማና መቀሌ እንገኛለን፡፡
ላይፍ ኃ/የተ/መ/ ቁጠባና ብድር የህብረት ስራ ማህበር!
ቁጠባ ለተሻለ ነገ!!!
ለአጭር የፅሁፍ መልዕክት 6198
መልካም አዲስ ዓመት!!
፳፻፱ 2019


ቡና ባንክ
BUNNA BANK
Bank of the Visionaries!
Happy New Year
2019
መልካም
አዲስ ዓመት





# እንኳን ለ2019 ዓ.ም አዲስ ዓመት አደረሳችሁ!

## የድርጅታችን ተሸላሚዎች እንኳን ደስ ያላችሁ!

ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት ህጋዊ ፈቃድ ኖሮት በሀገራችን በአምራችነትም ሆነ በአገልግሎት ሰጪነት የሰሩ ተቋማት ለሀገር እና ለህዝብ ለሰሩት ስራ ምስጋና፣ ሽልማትና እውቅና በመስጠት የላቀ ስራ በመስራት እንዲዘልቁ ለማድረግ የተቋቋመ ብቸኛ የሽልማት ድርጅት ነው። ድርጅታችን ላለፉት 32 ዓመታት በነበሩት ሽልማቶች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኦሮሚያ ባንክ፣ የካቲት12 ሆስፒታል፣ አባሃዋ ትሬዲንግ፣ የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ፣ አድማስ ዩኒቨርስቲ፣ ሀሌሉያ ሆስፒታል፣ አዲስ የመድኃኒት ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አሰር ኮንስትራክሽን፣ ስቲሊ አር ኤም ብረታ ብረት፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ ሙገር ሲሚንቶ፣ ቀርጫንሺ ግሩፕ፣ ሌሶ ኢትዮጵያ፣ ኤስሳራ ቡና ላኪ፣ ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ፣ አሚን ሆስፒታል፣ ዘመን ኢንሹራንስ፣ ታደሰ ደስታ አስመጪና ላኪ፣ ሮያል ፎም፣ ቲኬ ግሩፕ ማኑፋክቸሪንግ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢክፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ አስመንኃ/የተ/የግ/ማ፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎት እና ልማት ማኅበራት ህብረት፣ የኢትዮጰያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣ ኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ ኢንዲያና ት/ቤት፣ የኦሮምያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ፣ ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት፣ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ፣ ፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን ኢ.ማ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር፣ ኢፌድሪ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር፣ ጸሜክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢፌድሪ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት፣ ቀስተ ደመና ፕላስቲክ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ቤዛ ፓስቴሪቲ የልማት ድርጅት እና ሌሎችም ተሸልመዋል። የ2018 ዓ.ም ማጠናቀቂያም ዜና የተሰራላቸው የግራንድ አፍሪካን የተቋማትና አመራር ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 1 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። በተጨማሪም የእህት ኩባንያችን የወርልድ ክላስ የጥራት ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 8 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። ሌላው የሽልማት ድርጅታችን እህት ኩባንያ አቢሲኒያ የከፍተኛ ክብር የሎሬት ሽልማት ድርጅት በልዩ ድምቀት ህዳር 6 ቀን ግለሰብ ሎሬቶችን ይሸልማል።

**ለተጨማሪ መረጃ +251911 – 24 83 68 / +251911 – 24 23 88 ይደውሉ።**




**ትጉኃንን እንሸልማለን!!! ፳፻፲፱ | 2019**

## በተስፋ... ከገጽ 7 የዞረ

ሙሉ እምነት አለኝ። ይህ አዲስ ምዕራፍ እያንዳንዱ አባት፣ እናትና ወጣት ሀገሩን በጋራ ለመገንባት የሚያስችለውን አዲስ እይታና ተነሳሽነት እንዲይዝ እንደሚያደርገው አብራርተዋል፡፡

በተለይም በማህበረሰብ ደረጃ የተፈጠረው መቀራረብና የውይይት ባህል፣ በዜጎች መካከል የነበረውን ስጋት አስወግዶ በምትኩ አብሮ የመስራትና የመረዳዳት መንፈስ እንዲያብብ ያደርጋል። ሰዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው፣ በንግድ፣ በትምህርትና በማህበራዊ እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ የሰላምን ዋጋ በደንብ ተረድተው ለተግባራዊነቱ እንዲሰሩ አቅም ይሆናቸዋል። ይህም አዲሱን ዓመት የተሻለ የስራ፣ የዕድገትና የብልፅግና ጊዜ ለማድረግ በሁሉም ዘንድ ትልቅ ህልምና ተስፋ እንዲሰነቅ አስችሏል።

በመሆኑም ወደ 2019 ዓ.ም የተደረገው ሽግግር የዓመት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የዜጎች ስነ-ልቦና እና የሀገር አቅጣጫ የታደሰበት ታሪካዊ አጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያውያን የገጠሟቸውን ፈተናዎች በውይይት የመሻገር አቅማቸውን ያስመሰከሩበት ወቅት ነው፡፡ አዲሱ ዓመት የእውነተኛ አንድነት፣ የፍትህ እና የጋራ ብልፅግና ዘመን እንደሚሆን ይታመናል። ይህ የተስፋ ወጋገንም ሀገሪቱን ወደ ተሻለና ወደ ተረጋጋ የወደፊት ምዕራፍ ለማሸጋገር አቅም ይሆናል፡፡

"ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል" እንዲሉ ኢትዮጵያውያን በምክክር ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ለእኛም፣ ለሀገርም፣ ለቀጣዩ ትውልድም ማበጀት የሚያስችል ስራ ሰርተዋል፡፡ ይህ ትልቅ የተስፋ ስንቅ ነው፡፡ አዲሱ ዓመት የዓመተ ምህረት ለውጥ ብቻ አይደለም የተባለውም ለዚሁ ነው፡፡ በያዝነው አዲስ ዓመት ተስፋችን ወደ ተጨባጭ ውጤት እንዲቀየር፣ የምንሻው ዘላቂ ሰላም እና ብልፅግና እንዲረጋገጥ ሁላችንም የበኩላችንን ልንወጣ ይገባል እያልን መልካም አዲስ ዓመት እንዲሆንላችሁ ተመኘን፡፡

## ከበዓላት... ከገጽ 12 የዞረ

ለተቸገሩት ማካፈል የደስታ ምንጭ ነው። ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ማህበረሰቡ በተቻለ መጠን ካለው ላይ በመቀነስ ማካፈል ይኖርበታል። በተለይ ደግሞ ጎረቤቶችን እና በሰፈር የሚኖሩ ዜጎችን መጎብኘት፣ ችግራቸውን በመካፈል ማቃለል እና እንዲደሰቱ ማድረግ ያስፈልጋል"።

በበዓላት ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ መንግስት፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና ባለሀብቶች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የሚያደርጉት ማዕድ ማጋራት ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳለው ደሳለኝ (ዶ/ር) ያነሳሉ። እነዚህ አካላት የሚያደርጉትን መልካም ተግባር በማየት ሌላውም ወገን አርዓያነታቸውን በመከተል የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት ይነሳሳል። ከዚህ ባሻገር የሚሰጠው እየበዛ፣ የሚቀበለው ደግሞ እያነሰ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል። አሁን ባለው ሁኔታ ድጋፍ የሚሻ የማህበረሰብ ክፍል ቀላል የሚባል አይደለም። በተለይ በበዓል ወቅት ዜጎች ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ ድጋፍ ያስፈልጋል። በመሆኑም ድጋፍ የሚሹ ዜጎች የሚረዱበትን እና ድጋፉ የሚደርስበትን መንገድ በተደራጀ መልኩ መዘርጋት እንደሚገባ ይመክራሉ።

የመደጋገፉ እሴት ከስግብግብነት፣ ስርቆት፣ ሙስና እና የተለያዩ ችግሮች አንፃር እየተሸረሸረ ቢመጣም አሁንም እንዳልጠፋና ወደፊት እንደሚቀጠል የሚያነሱት ደሳለኝ (ዶ/ር)፣ ይህ እሴት እንዲጎለብት ራስ ወዳድነትን፣ ስርቆትን፣ ግጭትንና የመሳሰሉትን እንቅፋቶች ማስወገድ ያስፈልጋል። ለዚህም ሰላም እንዲፈጠር መስራት፣ ልማትን ማጠናከር እና የህዝብ ቁጥር እድገትን መመጠን ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

የሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህርና ተመራማሪው ገብሬ ይንቲሶ (ፕ/ር) በበዓል ሰሞን ሊኖር ስለሚገባው መደጋገፍና መረዳዳት በተመለከተ ባለፈው ጥር ወር ለዝግጅት ክፍላችን እንዳጋሩት፣ የተቸገሩትን መደገፍና በጎ ማድረግ በበዓል ቀን ብቻ የምናደርገው ሊሆን አይገባም። በበዓል ወቅት ከሚደረገው የማዕድ ማጋራትና ሌሎች ስጦታዎች በተጨማሪ ባህላችንም ውስጥ ስላለ፤ በሌላውም ቀን፣ አቅም ለሚያንሳቸው ወገኖች ድጋፍ ማድረግና ራሳቸውን የሚችሉበት ሁኔታ ለመፍጠር መስራት ይገባል። በዚህ ረገድ ከታች ጀምሮ ልጆች ጥሩ ስብዕና ተላብሰው እንዲያድጉ ማስተማር ይገባል፡፡ ስለ መልካምነት፣ ቸርነት፣ ልግስና፣ ትብብር ማስተማር ያስፈልጋል። ይህ ሲደረግ በጎ ማድረግን እየተላበሱ፣ መደጋገፍና መተባበርን ባህል እያደረጉት እንዲሄዱ ያደርጋል፡፡ በማህበረሰብ መካከል ያለው ትብብርና ትስስርም ይጠናከራል፡፡ በማህበረሰብ ዘንድ ያሉትን ነባር እሴቶች በማጠናከር በጎ ማድረግ ወሳኝ የመረዳዳት ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ መስራት ይገባል፡፡

## እቅዶቻችንን ... ከገጽ 14 የዞረ

በመፈተሽ እንደገና ማስተካከልና ማሻሻል ያስፈልጋል።

የውጭ አገር የስነ ልቦና ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በአዲስ ዓመት እቅዶች ዙሪያ ያደረጓቸው ጥናቶች፣ አብዛኛዎቹ ሰዎች የሚያቅዷቸውን ግቦች እስከ መጨረሻው ማሳካት እንደሚያቅታቸው ያረጋግጣሉ። በአሜሪካው ስክራንተን ዩኒቨርሲቲ ስመጥር የስነ ልቦና ፕሮፌሰር ጆን ኖርክሮስ "Making Resolutions That Stick in the New Year" በሚል ርእስ እ.ኤ.አ በ2018 ባካሄዱት ጥናት፣ አዲስ ዓመት ሲመጣ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች እቅድ ያቅዳሉ፡ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ስኬታማ የሚሆኑት ከ8 እስከ 9 በመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። ተመራማሪዎቹ እንደሚገልጹት፣ የአብዛኞቹ ሰዎች እቅድ ከጥቂት ወራት በኋላ የመሰናከል አዝማሚያ ያሳያል።

እንደጥናቱ የእቅዶች አለመሳካት ከግብ አወጣጥ ዘይቤ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የሆነን መጥፎ ልማድ ለመተው የሚያቅዱ ሰዎች (ለአብነት፡ መጠጥ አቆማለሁ፣ ጫት አልቅምም፣ ገንዘብ አላባክንም... የሚሉ) ይበልጥ እቅዳቸው ያለመሳካት ዕድል አለው። በአንጻሩ አዲስና አወንታዊ ልማድን ለመተካት የሚያቅዱ ሰዎች (ለአብነት፡- የአልኮል መጠጥ እቀንሳለሁ፣ ዛሬ አልጠጣም፣ በዚህ ሳምንት አልጠጣም፣ በሳምንት አንድ ቀን ስፖርት መስራት እጀምራለሁ... በማለት የሚያቅዱት) የበለጠ እቅዳቸውን የማሳካት እድላቸው ከፍተኛ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። ምክንያቱም ቀስ በቀስ በራስ መተማመናቸው ስለሚጨምር ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች እቅድ ሲያቅዱ ትልቅ ችግርን ከመጋፈጥ የተወሰነ ዞር አድርገው ሊሳካ በሚችል መንገድ ማቀድ አለባቸው።

በአጠቃላይ የስነ ልቦና እና የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ማቀድ ያለብን የምናሳካውን ነገር ነው፡፡ መኪና እገዛለሁ ብለን ስናቅድ "ገቢያችን ስንት ነው?" ብለን ማሰብ አለብን፡፡ ገቢያችን ትንሽ ከሆነ ቤት ወይ መኪና እገዛለሁ ብለን ሳይሆን ከማገኘው ገቢ ላይ ለቀጣይ መኪና ወይ ቤት መግዣ የተቀሰነ ገንዘብ አቆጥባለሁ የሚል እቅድ ነው መታቀድ ያለበት፡፡ ግን ደግሞ ለምናስመዘግባቸው ትንንሽ ስኬቶች እንኳን ሳይቀር ለራሳችን እውቅና መስጠትና ራስን ማበረታታት እንደሚገባ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ለውጥ በሂደት የሚመጣ ረጅም ጉዞ በመሆኑ፣ በራሳችን ላይ ትዕግስት ሊኖረን ይገባል። ያልተሳኩ እቅዶችን ምክንያት በመለየትና ስህተቶችን በማረም ወደፊት መቀጠል ለተሻለ ስኬትና ለስነ ልቦና ጤንነት መሰረት ነው።

# ማስታወቂያ

ወ/ሮ ግርማዊት ኢሳያስ ጊደይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000060300435 ሴሪ ቁጥር L 0203246 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የካርታ ቁጥር W2/2/18/228/609/11210/01 ሴሪ 0247559 የሆነው በአቶ እንዳለ ምራኒ ያሲን ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 02/13/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያሳወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 499 የይዞታ የሆነው ስም የተመዘገበው በአዲሱ የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020500514 ሴሪ ቁጥር R 0152896 በቀድሞው የካርታ ቁጥር አከ/063/ስዝ እና ሴሪ ቁጥር 006618 በእነ ወ/ሮ ደንበሌ ወልደኪዳን አባኖ (6 ሰዎች) (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 28/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090704184 በአቶ ፍሬው ለማ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 29/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ**
**ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ልኡል ሀይሉ በቀን 25/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወራዳ 9 ክልል ውስጥ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/17/6/19/160503/00 የሆነ ኦርጂናል ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲጻፍልኝ ሲሉ አመልክተዋል። በመሆኑም ካርታው የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፣ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት**
**ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አያን ኢብራሂም አብዱራህማን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060600340 የሚገኘው መኖሪያ ቤት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ ሴሪ ቁ L0284953 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**




እኔ ወ/ሮ በለጡ መስቀሌ ቡታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 06 የይዞታ (የቤቱ) ልዩ መለያ ኮድ ቁጥር AA000091502644 የተሰጠበት ቀን 18/02/2017 ዓ.ም ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለው /ይዠዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር ሴሪ ቁጥር C0282850 ይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502542001050‌05 ይመኙሻል ዱባሳ ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በሴሪ ቁጥር R 003398 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000010300512 በ ሰርፀ ሀበተወልድ ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የጠፋብኝ በመሆኑ ምትክ ይሰጠኝ በማለት ያመለከቱ በመሆኑ ይኸው የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በእኔ እጅ ይገኛል ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 1381/2017 አንቀፅ 36 (3) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲያመለክት ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ 10-1/107/9/1/8997/00 ሴሪ ቁጥር 1445625 በአደይ አበባ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ

ከላይ በርእሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ እነ ዘውዴ መገርሳ አያና ስም የተመዘገበ ኮንዶሚንየም መለያ ቁጥሩ AA000050400343 የሆነና የተሰጠበት ቀን 03/12/2017 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የጠፋባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ በቁጥር የካፓ/ለ/ሂ/2318/18 በ28/12/2018 ዓ.ም የተጻፈ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ትራኮን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ ወረዳ 01 ውስጥ የሚገኝ ይዞታ /ቤት/ ካርታ ቁጥር ድ/37/98/24584/10095/02 ሴሪ ቁጥር 031697 በስማቸው የተመዘገበ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በእነ ማሬ ገበየሁ (4 ሰዎች) ስም በቀድሞ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 በአዲሱ ክ/ከተማ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 08 በካርታ ቁጥር 03/85/9055/00 ሴሪ ቁጥር 006925 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 25/12/2018 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፤ ስለዚህ የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዠዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ወ10/ገ/ጉ/ጤ/ጣ/ግ/ጨ/001/2019 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት የገላን ጉራ ጤና ጣቢያ የ2019 ዓ.ም በጀት ዓመት ሎት 1:- ቋሚ እቃ ሎት 2:- የደንብ ልብስ ሎት 3:- አላቂ የፅዳት እቃዎች ሎት 4:- አላቂ የቢሮ እቃዎች ሎት 5:- ልዩ ልዩ ማሳሪያዎች ሎት 6:- የህትመት ስራዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሰረት ተጫራቾች**

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ። ጥቃቅንና አነስተኛ በራሳቸው ሰርተው ለሚያቀርቡ እቃዎች ብቻ የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጨራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን በየሎቱ በመለየት ፖስታ ላይ በመግለፅ አሽገው ኦሪጅናል እና ኮፒ ብለው በመፃፍ ለይተው የድርጅታቸውን ማሕተም እና ፊርማ በማድረግ በጤና ጣቢያው የግዢ ቡድን ቢሮ ቁጥር -405- ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጨራቾች ለጨረታው የተዘጋጀውን ሰነድ በየሎቱ የማይመለስ 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል በጤና ጣቢያው የግዢ ቡድን ቢሮ ቁጥር -405- መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. ይህ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት አየር ላይ የሚውል ሲሆን የጨረታው ሳጥን በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ሲሆን ምናልባት 11ኛው ቀን የህዝብ በዓል ወይም ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጭ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
6. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተመሰከረለት ቼክ ወይም CPO መጨረሻ ተመላሽ የሚሆን ለሎት 1:- ቋሚ እቃ 34000 ለሎት 2:- የደንብ ልብስ 25000 ለሎት 3:- አላቂ የፅዳት እቃዎች 21000 ለሎት 4:- አላቂ የቢሮ እቃዎች 8000 ለሎት 5:- ልዩ ልዩ መሳሪያዎች 2000 ለሎት 6:- የሕትመት ስራዎች 5000 ማስያዣ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጸው ሙሉ ዝርዝር ሁኔታ የጨረታው መመሪያ ሆኖ ችግሮች ካጋጠሙ በጊዜው መመሪያ የሚዳኝ ይሆናል፡፡
8. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. የጨረታ ዋጋ የሚሞላው በተቀመጠለት መለኪያ ብቻ ሲሆን ከመለኪያው ውጪ የተሞላ ዋጋ እንዲሁም ስርዝ ድልዝ ወይም በፍሉድ የተነካካ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ከጨረታው ውድቅ ይደረጋል፡፡
10. ተጨራቾች ለሚጫራቱት እቃዎች ሙሉ በሙሉ ናሙና ማቅረብ እና በሚያቀርቡት ናሙና ላይ ምልክት ወይም ድርጅቱን የሚገልጽ ምልክትም ሆነ ማሕተም ማድረግ የለባ ቸውም፡፡ ተጨራቾች የሚያቀርቡት ናሙና ከሚያስገቡት እቃ ጋር ፍጹም የተለየ መሆን የለበትም፡፡
11. ጨረታውን አሸነፊ ሆነው ከተገኙ በኃላ 10% ባሸነፉት እቃ መጠን የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
12. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በተጨማሪ ለማብራሪያ ጥያቄ ለጨረታው ከቀረቡ የእቃዎች ዝርዝር ውስጥ መ/ቤቱ እስከ 25 በመቶ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር:- 0901259401/0975995034 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**
**አድራሻ:- ከጎሮ ወደ ኮየ በሚወስደው መንገድ ከ11 አደባባይ 2 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ**

**በአቃ/ቃ/ክ/ከ/ወ10 ገላን ጉራ ጤና ጣብያ**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የገላን ጉራ ጤና ጣቢያ**

## የቅጥር ማስታወቂያ

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የ ሥ ራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የቴሌቪዥን ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የቴሌቪዥን ስፖርት ዜና አቅራቢ | | ቢኤ/ ኤም.አዲግሪ | 0/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ የውጭ ቋንቋ ወይም በተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ | -- | 3 | በፈሊራንስ | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው በወጣው ክፍት መደብ በቴሌቪዥን ስፖርት ዝግጅት እና ዜና አንባቢነት መሆን አለበት፡፡
4. የምዝገባው ቀን ከመስከረም 04 ቀን 2019 ዓ.ም እስከ መስከረም 15 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ
5. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
6. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት/5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111 55 18 48

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

# የአውደ ዓመት ትዝታ እና ሙዚቃ

**በአብርሃም ገብሬ**

የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት የሚለየው በትውስታው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሙሉ በሙሉ ትውስታውን ሲያጣ እሱነቱን ከማጣት አይተናነስም፡፡ ሰው በዚህ የትውስታው ባህር እየቀዘፈ፣ በትዝታ ወደ ኋላ ያቀናል፡፡ በዚህ የትዝታ ማህደሩ ውስጥ አንድም ሃዘኔታ ያጠላበት፣ አንድም ሃሴት የሞላበት ትውስታዎች ይዟል፡፡ አንድም ጸጸት የሞላበት፣ አንድም እንደ ወይን የጣፈጠ ጣዕም በጉያው ሸሽጓል፡፡ ከእነዚህ ውብ ትዝታዎቻችን መካከል የበዓል ሰሞን እንቅስቃሴ አንዱ ነው፡፡

አዲስ ዓመት (ዕንቁጣጣሽ)፣ ልጅነትና ትውስታችን በብዙ መንገድ ጥብቅ መስተጋብር አላቸው፡፡ ዕንቁጣጣሽ በመጣ ቁጥር ልጆች ደስታቸው መልከ ብዙ ነው፡፡ ሴት ልጆች አበባየሆሽን ይጨፍራሉ፡፡ በየሰው ቤት ደጃፍ ላይ ቆመው ከዓመት ዓመት እንኳን አደረሳችሁ ብለው መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ። ቀጣይ ዕንቁጣጣሽም በፍስሃና በሀሴት ያደርሳቸው ዘንድ ለሚጨፍሩበት አባወራ ወይም እማወራ ይመኛሉ፡፡ በዚያውም የተሳጣቸውን ሳንቲም ወይም ዳቦ ይዘው ወደ ሌላኛው ቤት ያዘግማሉ፡፡ ይሄ እንቅስቃሴ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ መገኘታችንን ያበስራል፡፡

ሌላው አዲስ ዓመትን የትዝታችን ሁነኛ ማዕከል የሚይዘውና ትክክለኛ የበዓል ድባብ የሚፈጥረው ደግሞ ሙዚቃ ነው። በተለያዩ ጊዜያት የተቀነቀኑ የዓውደ ዓመት ሙዚቃዎች የአዲስ ዓመት መቃረብ አብሳሪ ደወሎች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የታላቁ ሙዚቀኛ ጥላሁን ገሰሰ "ዓውደ ዓመት" የተሰኘው ሙዚቃ የአዲስ ዓመት መምጣትን ያበሰረ፣ ድባቡን ቁልጭ አድርጎ ያሳየና በብዙ ሰው ልብ ውስጥ ትዝታን ያኖረ የጥበብ ስራ ነው፡፡

የፀሐይ ብርሃን ደምቃ

ክረምትና በጋ

የዘመን ቀመር ያላት

የአስራ ሶስት ወር ጸጋ

ወግና ልማዳችን የወረስነው ከአበው

የዓውደ ዓመቱ ትዝታ አይጠፋም ህያው ነው፡፡

እንኳን አደረሰን ሲባባል ወዳጅ ጎረቤቱ

ትዝታው መቼ ይጠፋል አቤት ማስደሰቱ...

ወርሃ መስከረም ከጭጋጋማው የክረምት ወራት ወደ ፀሐያማው፣ አበባ ወደሚያብብበት የሚደረግ ሽግግር ነው። መስከረም አንድ ብሎ ሲጀመር ነው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚለወጠው፡፡ ሙዚቀኛው በጥቂት ስንኞች የኢትዮጵያን ለየት ያለ የዘመን አቆጣጠር (የ13 ወራት ጸጋነት) ከወቅቱ የተፈጥሮ ውበት ጋር አጋምዶ ያቀርበዋል።

መስከረም የተስፋ ወር ነው፤ ክረምቱ አልፎ በጋው ሲተካ፣ ተፈጥሮ አዲስ


ፎቶ፡- ከገፀ ድር
ዘመን አይሽሬ የአውደ ዓመት ዘፈን ካበረከቱልን መካከል ጥቂቶቹ

ልብስ እንደምትለብስ ሁሉ የሰው ልጅ መንፈስም አዲስ ተስፋን ይሰንቃል። በዚህ የጥላሁን የሙዚቃ ስንኞች ውስጥ የበዓል ትዝታ የአዲስ ዓመት ለውጥ ሳይሆን፣ ከቀደሙት አባቶች የተወረሰና ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ የማይጠፋ ህያው እሴት እንደሆነ ይጎላል። ከዚህ አንጻር አዲስ ዓመትን አጉልተው ከሚያሳዩና ትዝታን ከቀረጹ ሙዚቃዎች መካከል አንዱ ሆኗል፡፡

አቤት በአዲስ ዓመት ዘመኑ ሲለወጥ

የአበቦቹ ሽታ መዓዛው ሲያውድ

ኮበሌውም ሲጨፍር ሲል መስከረም ጠባዬ

ኮረዳዋን አጅቦ ሲዞር ሰፈር ቀዬ...

እያለ ጥላሁን ገሰሰ በዚህ ሙዚቃው ዓውደ ዓመትን ይኩላል፡፡

መስከረም አደይ አበባ ምድርን በውበት መጎናጸፊያ የምትሸፍንበትና የተፈጥሮን መዓዛ የምንምግበት ወቅት ነው፡፡ በዕንቁጣጣሽ ወቅት ሴት ልጆች "አበባየሆሽ" እያሉ ሲጨፍሩ፣ ወንዶች ልጆች ደግሞ "ሆያሆዬ" ወይም የበዓሉን መምጣት የሚያበስሩ ዜማዎችን እያዜሙ ሰፈር ለሰፈር ይዞራሉ። በጥላሁን የሙዚቃ ስንኞች ውስጥ የሰፈረው ሃሳብ ዛሬም ድረስ ያልደበዘዘው ዓውደ ዓመትና ልጅነትን የሚዘክርና ትዝታው ከዘመን ዘመን የሚሸጋገር ነው፡፡

አዲስ ዓመትን ስናስብ ቀድሞ ወደ አዕምሮአችን በፍጥነት የሚመጣው ሌላኛው ዘመን አይሽሬ ሙዚቃ የዘሪቱ ጌታሁን "ዕንቁጣጣሽ" የተሰኘው የጥበብ ስራ ነው፡፡

እንቁጣጣሽ

እንኳን መጣሽ

በአበቦች መሃል

እንምነሽነሽ

መስከረም ጠባ... አበባ

እሰይ እሰይ አበባ...

የዘሪቱ ጌታሁን "ዕንቁጣጣሽ" የተሰኘው ሙዚቃ የአዲስ ዓመት መምጣትን አብሳሪ ዜማ ነው፡፡ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን የልጅነት ትዝታ ከሚቀሰቅሱ ዘመን አይሽሬ የባህል ዜማዎች መካከል ቀድሞ የሚጠቀስ ሥራ ነው። ይህ ሙዚቃ በተለይም የሴት ልጆችን የበዓል ጨዋታ፣ የአበባየሆሽን ድባብና የመስከረምን ለምለምነት ያቀፈ ዘመን አይሽሬ የጥበብ ሥራ ነው፡፡ ሙዚቃውን መንገድ ስንጓዝ ባጋጣሚ ብንሰማው ብዙ ትዝታዎችን ጎትቶ የሚያመጣ ድንቅ ዜማ ነው፡፡ መሰል የዓውደ ዓመት ሙዚቃዎች ትዝታን በማሻገር ረገድ የሚስተካከላቸው የጥበብ ዘርፍ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ሌላው በዓል በመጣ ቁጥር ከምናዳምጣቸው እጅግ ተወዳጅ ሙዚቃዎች መካከል አንዱ የገነት ማስረሻን "ዓውደ ዓመት" የተሰኘው ሙዚቃ ነው፡፡ በዚህ ሙዚቃ ውስጥ የበዓል አከባበር ለኢትዮጵያውያን የአንድ ሰሞን ፌሽታ ሳይሆን የማንነታቸው መገለጫ፤ የእሴቶቻቸው መከሰቻ መሆኑን በውብ ዜማ እንዲህ ከይነዋለች፡-

እሰይ ደስ ይበለን...፤ ዓውደ ዓመት መጣልን፡፡

ዓውደ ዓመት በዓል ሲመጣ፤ ዓውደ ዓመት ጊዜን ጠብቆ...

ዓውደ ዓመት መፈቃቀሩን፤ ዓውደ ዓመት ደስታን ሰንቆ...

ዓውደ ዓመት ዘመድ አዝማዱ፤ ዓውደ ዓመት ይሰባሰባል

ዓውደ ዓመት ወገን ለወገን፤ ዓውደ ዓመት ይተሳሰባል፡፡...

ዘፋኟ በዚህ ሙዚቃዋ የበዓልንና የማህበረሰቡን ጥብቅ መስተጋብር ነው ኪነ ጥበባዊ በሆነ መንገድ የምታስቃኘው። ለኢትዮጵያውያን የበዓላት ትልቁ ፋይዳ አሰባሳቢ መሆናቸው ነው። የተራራቁ ዘመዶች የሚገናኙበት፣ የተጣሉ የሚታረቁበት፣ ሀብታሙና ደሀው በጋራ ማዕድ የሚቀመጡበት የማህበራዊ መስተጋብር መድረክ ነው። የገነት ሙዚቃም ይህን ነው አጉልቶ የሚያሳየው።

"የኛስ ዓውደ ዓመት፣ በጣም ይደምቃል፣

በደስታ መንፈስ፣ ልብን ይሰርቃል፣

ለዚህ ያበቃን ፈጣሪ ያውቃል፡፡

በዓውደ ዓመትማ ምን ይጠየቃል

ቤቱም ይሞቃል ያሸበርቃል..." እያለች ሙዚቀኛ ገነት ስታቀነቅን፣ ስንኞቹ ውስጥ በዓላትና ሙዚቃ፤ በዓላትና ማህበረሰቡ ያላቸውን ጥብቅ ትስስር በማውሳት ጭምር ነው፡፡ በበዓላት ሰውና ቤቱ ብቻም ሳይሆን ተፈጥሮም ትደምቅ የለ!... ሙዚቀኛዋም ይህን የማህበረሰቡን ነባራዊ የበዓል አከባበርና አንድምታ ኪነ ጥበባዊ አድርጋ አቅርበዋለች፡፡

የበዓልን መድረስ ከሚያበስሩና ከሚያደምቁ ሙዚቀኞች መካከል አንዷ ማንአልሞሽ ዲቦ ነች ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በተለይ ስለ ዓውደ ዓመት ያቀነቀነችው ሙዚቃ በብዙዎቻችን የበዓል ሰሞን ትውስታ ላይ ጉልህ ቦታ ይዞ ይገኛል።

"ጤና ለሰጠው ሰው እድሜውን ላደለዉ

ዓውደ ዓመት ደስታ ነው፤ ዓውደ ዓመት ፀጋ ነው" ብላ በምትጀምረው የዓውደ ዓመት ዘፈኗ ውስጥ የኢትዮጵያውያንን የበዓላት አከባበርና እሴቶች አጉልታ የምታሳይበት ስራዋ ነው፡፡

"የማር ጠጅ ወለላ፣ ዳቦውና ጠላ፣

ሲበላ ሲጠጣ፣ ዓውደ ዓመት ሲመጣ፣

እንዴት ነው ዘንድሮ፣ ስንት ገባ ዶሮ፣

በአስራ ሁለት ብልት፣ ሲለካ ሴትነት" ስትል፤ በበዓል ቀናት የሚደረጉ ህዝባዊ ክዋኔዎችና የአመጋገብ ዘይቤዎችን በውብ ዜማ በማቅረብ የሙዚቃ ውለታን ይበልጥ አጉልታ አሳይታለች፡፡

ከላይ በወፍ በረር እንደቃኘነው አዲስ ዓመትን ከሚያደምቁ፣ ትዝታን ከሚቀሰቅሱ ኩነቶች መካከል ስለ ዓውደ ዓመት የተቀነቀኑ ዜማዎች ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ሙዚቃዎች እንደየባህሉና ቋንቋው የተወሰነ ልዩነት ቢኖራቸውም፣ ዋነኛ ጭብጣቸውና ማጠንጠኛቸው ግን በዓል ደስታን ይዞ መምጣቱ፤ የተራራቀውን ዘመድ አዝማድ እንዲቀራረብ ምክንያት መሆናቸው የጋራ መገለጫቸው ነው፡፡ እንዲሁም በዓላት የዕርስ በዕርስ መረዳዳቱ ይበልጥ ጎልቶ የሚታይባቸው በመሆኑ፤ በተለያዩ የሀገራችን ባህሎች ውስጥ የተቀነቀኑ ሙዚቃዎች ይበልጥ የኢትዮጵያውያን ጥብቅ የአብሮነት መስተጋብር የሚታይባቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከምንም በላይ ግን አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋን የምንሰንቅበት በመሆኑ፣ የሙዚቃ ዜማዎቹ ይህ ተስፋ ዘመን እንዲሻገር ያደርጋሉ፡፡ ከሙዚቃ ባሻገር በስነ ጽሑፍ ውስጥም አዲስ ዓመትን የሚያወሱ ድርሰቶች አሉ፡፡ ለአብነትም በጋዜጠኛና ደራሲ ዘነበ ወላ የተጻፈው "ልጅነት" በተሰኘው የአጫጭር ልብ-ወለዶች መጽሐፍ ውስጥ "ዕንቁጣጣሽ" እና በጋዜጠኛና ደራሲ መስፍን ሃብተ ማርያም የተጻፈው "አውዳመት" የተሰኘው አጭር ድርሰት ይጠቀሳሉ፡፡